ልውጠት እና ቅጥለት በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ላይ በተዜሙ የቃል ግጥሞች፣ ንጽጽራዊ ትንትና[1]

መስፍን መሰለ[2]

አኅጽሮተ ጥናት

በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የተዜሙት የቃል ግጥሞች በተለያዩ ጸሓፍት ከመመዝገባቸው በፊት እየተለወጡ እንደተላለፉ ቢታመንም እንዴት እና ለምን እንደተለወጡ ንድፈሐሳባዊ መላምት እንጂ ተጨባጭ ማስረጃ ማቅረብ አልተቻለም። መላምቱ መነሻ ያደረገው የቃል ግጥሞቹ በቃል ሲተላለፉ ማስታዎስ ባለመቻሉ ወይም ኾን ተብሎ ሊለወጡ ይችላሉ ከሚል የንድፈሐሳብ ግዛቤ ነው። የቃል ግጥሞቹ በቃል ሲተላለፉ ተለውጠዋል ተብሎ እንደሚታመነው ኹሉ በጽሑፍ ከተመዘገቡ በኋላም ተለውጠዋል። በጽሑፍ በተመዘገቡት የቃል ግጥሞች ልውጠት እና ቅጥለት ላይ ጥናት ባለመደረጉ ይኽንን ጥናት ማካኼድ አስፈልጓል። የጥናቱ ዋና ዓላማም በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ላይ የተዜሙ የቃል ግጥሞችን ልውጠት እና ቅጥለት መመርመር እና መተንተን ነው። በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ላይ የተዜሙ የቃል ግጥሞችን ልውጠት እና ቅጥለት ማጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች አሉት። በቃል ግጥሞቹ ምን ምን ልውጠቶች እንደ ተከሰቱ ለመገንዘብ ያስችላል፤ የቃል ግጥሞቹ የልውጠታቸውን ምክንያቶች እና ቅጥለታቸውን ለመገንዘብ ያስችላል፤ የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ታሪክ በቃል ግጥሞቹ ምን ያኽል እንደተንፀባረቀ ለመረዳት ያስችላል፤ የቃል ግጥሞቹን በታሪክ መረጃነት በመጠቀም ኺደት ሊደረግ የሚገባውን ጥንቃቄ ያስገነዝባል። በተለያዩ ጸሓፍት ተለዋውጠው የተመዘገቡ የቃል ግጥሞች የተመረመሩት እና የተተነተኑት ቅርጻቸውን እና ይዘታቸውን፣ የተዜሙበትን ጊዜ እና ቦታ በማነጻጸር ነው። ከጥናቱ ውጤት መረዳት እንደሚቻለው የቃል ግጥሞቹ የምእላድ እና የቃላት አጠቃቀም፣ የሐረግ እና የሥንኝ አደራደር ልውጠት ይስተዋልባቸዋል። በተጨማሪም በአንዳንዶቹ የቃል ግጥሞች የቅርጽ ብቻ ሳይኾን የይዘትም ልውጠት ይታይባቸዋል። በጥቂት የቃል ግጥሞች የሚታየው የይዘት ልውጠት በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የተፈጸመን ታሪክ እንደሚቃረን ለመገንዘብ ተችሏል። ስለ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የተዜሙት የቃል ግጥሞች በተለያዩ ምክንያቶች ኹሉም አልተመረመሩም፣ አልተተነተኑም። በዚኽ ጥናት ያልተመረመሩትን የቃል ግጥሞች የፎክሎር፣ የሥነጽሑፍ፣ የታሪክ እና የሥነ ሰብእ ተመራማሪዎች ትኩረት በማድረግ መመርመራቸው በሙያ መስኩ ሊኖር የሚገባውን ዕውቀት ያሰፋል፤ ያጎለብታል።

ቁልፍ ቃላት፡- ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ፣ የቃል ግጥም፣ ልውጠት፣ ቅጥለት፣ ንጽጽር

---

[1] ይኽን ጥናት ለማሻሻል በጥናት አቅራቢው የሚታወቁም፣ የማይታወቁም ተመራማሪዎች የተሰጡ ገንቢ አስያየቶች አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው። የመጀመሪያው ረቂቅ እንድከለስ አስተዋጽዖ አድርገዋልና ይመስገናሉ።

[2] በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም የፎክሎር እና ሥነ ጽሑፍ ተመራማሪ ነው። አድራሻው፡- ስልክ ቁጥር፡- +251 (0) 911614482፣ Email: mesfinmessele2002@ yahoo.com or /mesfin.messele@aau.edu.et.

1) የጥናቱ ዳራ

በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ታሪክ ላይ ትኩረት ካደረጉ የተለያዩ ጸሓፍት መካከል የተወሰኑት በእሳቸው ላይ ወይም ስለ እሳቸው የተዜሙ የቃል ግጥሞችን መዝግበዋል። ጸሓፍቱ ቃል ግጥሞቹን የመዘገቡት፣ በታሪክ ማስረጃነት፣ አንድም "እንዲህ ተብሎ ተገጠመላቸው" ለማለት ነው፤ አንድም፣ ስለ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የተዜሙትን የቃል ግጥሞች በቃል ግጥሞች ስብስባቸው ውስጥ ለማካተት ነው። ጸሓፍቱ በመዘገቧቸው የቃል ግጥሞች ላይ የተለያዩ ጥናቶችን ማካኼድ ይቻላል። ሊካኼዱ ከሚችሉ ጥናቶች መካከልም ይኽ ጥናት ትኩረት ያደረገበትን በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ላይ የተዜሙ የቃል ግጥሞችን ልውጠት እና ቅጥለት መመርመር እና መተንተን አንዱ ነው። በቃል ግጥሞቹ የሚታዩት ልውጠቶች እና ቅጥለቶች ከመመርመራቸው እና ከመተንተናቸው በፊት ከዚኽ ቀደም ለዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ በተዜሙ የቃል ግጥሞች ላይ የተካኼዱ ጥቂት ጥናቶች እንደሚከተለው በአጭሩ ተቃኝተዋል።

1. 1) የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

ስለ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ በተዜሙት የቃል ጥሞች ላይ ከተካኼዱ ጥናቶች መካከል፣ ታየ (Taye) (1983)፣ ፓንክረስት እና አስፋው (Pankhurst and Asfaw) (1985) እና መስፍን (2018 እና 2022 (እንደ ጎርጎሮሳዊ አቆጣጠር) (እ. ጎ. አ.)) ያቀረቧቸው ሥራዎች ይጠቀሳሉ። ታየ በጥናታቸው ትኩረት ያደረጉት የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን ታሪክ መሠረት አድርገው በተደረሱ የፈጠራ ሥራዎች ላይ ሲኾን ሰብአዊ ድርጊቶታቸው በፈጠራ ሥራዎች እንዴት በትእምርታዊነት እንደ ተገለጹ ሲያስረዱ ጥቂት የቃል ግጥሞችን ጠቅሰዋል። በቃል ግጥሞቹም የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የዐመፅ ተግባር፣ ደፋርነት እና ጀግንነት መንፀባረቃቸውን እና ተግባሮቻቸውም በእሳት፣ በነብር እና በአንበሳ መመሰላቸውን አስረድተዋል። የጥናታቸው ዋና ትኩረት የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን ታሪክ መሠረት ባደረጉ የፈጠራ ሥራዎች ላይ በመኾኑ በቃል ግጥሞቹ ላይ የታዩትን ልውጠቶች እና ቅጥለቶች አልመረመሩም። ይኽም ጥናታቸውን ከዚኽ ጥናት የተለየ ያደርገዋል።

ፓንክረስት እና አስፋው (1985) ለዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ በተዜሙ የቃል ግጥሞች ላይ ጥናት አካኺደዋል። ትኩረታቸውም ካፒቴን ቻርለስ ስፒዲ የተባለው እንግሊዛዊ በሰበሰባቸው እና በላቲን ፊደል በመዘገባቸው በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ወታደሮች በተደረደሩ የፉከራ ግጥሞች ላይ ነው። የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ወታደሮች በጦርነት ውሏቸው የፈጸሟቸውን የጀግንነት ተግባሮች እየዘረዘሩ በፉከራ ግጥሞች እንደሚያቀርቡ እና በአንድ አጋጣሚ የቀረቡትን የፉከራ ግጥሞች ወታደሮቹ አሻሽለው ወይም ለውጠው በሌላ አጋጣሚ ላይ እንደሚደረድሯቸው ገልጸዋል። የፉከራ ግጥሞቹ በቃል የሚተላለፉ በመኾናቸው አሻሽሎ ለሚፈለገው ጉዳይ መጠቀም የሚቻል መኾኑንም አስረድተዋል። ፓንክረስት እና አስፋው በጥናታቸው ትኩረት ያደረጉት በስፒዲ በተመዘገቡት የፉከራ ግጥሞች ላይ የሚታየውን የአጻጻፍ ግድፈት እንዴት ማስተካከል እንደሚቻል በማስረዳት ላይ ነው። አጥኚዎቹ ትኩረታቸው ባለመኾኑ በቃል ግጥሞቹ ላይ የሚታየውን የቅርጽ እና የይዘት ልውጠት እና ቅጥለት አልመረመሩም። ከዚኽም በላይ፣ ጥናታቸው ስፒዲ በሰበሰባቸው የፉከራ ግጥሞች ላይ የተገደበ በመኾኑ ለዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ በተዜሙት በርካታ የቃል ግጥሞች ላይ የሚታየውን ልውጠት እና ቅጥለት አልመረመሩም። በወታደሮች ፉከራ ግጥሞች ላይ ትኩረት

ማድረጋቸው እና በአንድ ሰው በተመዘገቡት የቃል ግጥሞች ላይ ራሳቸውን በመገደባቸው ጥናታቸው ከዚኽ ጥናት እንዲለይ አድርጎታል።

ከተጠቀሱት ጥናቶች ሌላ መስፍን (2018 እና 2022) ስለ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ በተዜሙት የቃል ግጥሞች ላይ ኹለት ጥናቶችን አቅርበዋል። መስፍን በ2018 (እ. ጎ. አ.) ባሳተሙት ጥናት በአዝማሪ በተዜሙ ዐሥራ አንድ የቃል ግጥሞች የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ጀግንነት እንዴት እንደ ተገለጸ ተንትነዋል፤ አስረድተዋል። ይኽ የመስፍን ጥናት በአዝማሪ ተዜሙ በተባሉት በጥቂቶቹ ላይ ብቻ የሚያተኩር በመኾኑ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮደስ የተሞገሱባቸውን ኹሉንም የቃል ግጥሞች አልመረመሩም። ከዚኽም በላይ፣ ጥናቱ የተሞጋሹ ጀግንነት በቃል ግጥሞች እንዴት እንደተንፀባረቀ እንጂ፣ ልውጠትን እና ቅጥለትን ባለመመርመሩ ከዚኽ ጥናት ይለያል።

መስፍን በ2022 (እ. ጎ. አ.) ባካኼዱት ሌላ ጥናት ለዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የተዜሙ የቃል ግጥሞችን ልውጠት መርምረዋል። ጥናታቸው ለዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ከተዜሙት ልውጠት ከሚታይባቸው የቃል ግጥሞች ብዛት አንጻር ሲመዘን፣ በጥናቸው አብዛኛዎቹን እንዳልመረመሩ መረዳት ይቻላል። የመስፍን ጥናት ልውጠት ከሚታይባቸው የቃል ግጥሞች መካከል በጥቂቶቹ ላይ ብቻ የሚያተኩር ከመኾኑም በላይ ቅጥለታቸውን አልመረመረም። ይኽም ባልተጠኑ ልውጠት እና ቅጥለት በሚታይባቸው የቃል ግጥሞች ላይ ጥናት ማካኼድ አስፈላጊ አድርጎታል። በቀደመው የመስፍን ጥናት በመረጃነት ያላገለገሉ ጥቂት የቃል ግጥሞች በዚኽ ጥናት ለተለየ ዓላማ ተጠቅሰው ተመርምረዋል፤ ተተንትነዋልም። ስለኾነም ይኽ ጥናት ልውጠት እና ቅጥለት በሚታይባቸው የቃል ግጥሞች ላይ በመመሥረት የቀረበ በመኾኑ ከቀደመው የመስፍን ጥናት ይለያል።

፲. 2) የጥናቱ ዓላማ እና ጠቀሜታ

የዚኽ ጥናት ዋና ዓላማ በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ላይ የተዜሙ እና በተለያዩ ጸሐፍት የተመዘገቡ የቃል ግጥሞችን ልውጠት እና ቅጥለት መመርመር እና መተንተን ነው። ከዋናው ዓላማ የሚመነጩ የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎችም፡- ፩ኛ) የቃል ግጥሞቹን ልውጠት ምክንያት ንድፈሐሳባዊ መላምትን እና መረጃን መሠረት በማድረግ መተንተን፣ ፪ኛ) የቃል ግጥሞቹን የቅርጽ እና የይዘት ልውጠት እና ቅጥለት መመርመር እና መተንተን፣ ፫ኛ) የቃል ግጥሞቹ በጽሑፍ ከተመዘገቡ በኋላ ልውጠታቸው መቀጠሉን ማስረዳት እና ፬ኛ) ተለውጠው በተመዘገቡት የቃል ግጥሞች የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ታሪክ በትክክል መንፀባረቁን ወይም አለማንፀባረቁን መመርመር እና ማስረዳት የሚሉት ናቸው።

ስለ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የተዜሙ ልውጠት እና ቅጥለት የሚታይባቸውን የቃል ግጥሞች ማጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች አሉት። ፩ኛ) በቃል ግጥሞቹ ምን ምን ልውጠቶች እንደ ተፈጠሩ ለመገንዘብ ያስችላል፤ ፪ኛ) የቃል ግጥሞቹን የልውጠት እና የቅጥለት ምክንያቶች ለመገንዘብ ያስችላል፤ ፫ኛ) የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ታሪክ በቃል ግጥሞቹ ምን ያኽል እንደተንፀባረቀ ለመረዳት ያስችላል፤ ፬ኛ) የቃል ግጥምን በታሪክ መረጃነት ለመጠቀም ሊደረግ የሚገባውን ጥንቃቄ ያስገነዝባል።

ልውጠት እና ቅጥለት የሚታይባቸው ስለ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የተዜሙ የቃል ግጥሞች የተሰበሰቡት ከተለያዩ ጸሓፍት ሥራዎች ነው። ጸሓፍቱም፦ ማኅተመ ሥላሴ (፲፱፻፷፩)፣ ገሪማ (፲፱፻፺፯)፣ ሥርግው ገላው (2008)፣ ተክለ ጻድቅ (፳፻፣ ፲፱፻፹፩ እና ፲፱፻፸፯)፣ ሥርግው ሐብለ ሥላሴ (2000)፣ ዓለማየሁ (፲፱፻፶፬ እና ፲፱፻፷፪)፣ ደስታ (፲፱፻፷፪)፣ የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ዜና መዋዕሎች ጸሓፍት እና ዓለሙ አጋ (በሲዲ ያሳተሙት የበገና መዝሙር) ናቸው። እነዚኽ የመረጃ ምንጮች የተመረጡትም ኾን ተብሎ ነው። የተመረጡበት ምክንያት የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን ታሪክ የጻፉ በመጽሐፎቻቸው፣ ማኅተመ ሥላሴ በቃል ግጥም ስብስባቸው ፣ ዓለሙ አጋ በበገና መዝሙራቸው፣ ዓለማየሁ ደግሞ ለማስተማሪያ ባዘጋጁት የግጥም መጽሐፍ ውስጥ ስለ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የተዜሙ ቃል ግጥሞችን መመዝገባቸው ወይም ማከተታቸው ቀድሞ ስለሚታወቅ ነው።

ከተጠቀሱት የመረጃ ምንጮች ፷ የቃል ግጥሞች ተሰብስበዋል። ከተሰበሰቡት የቃል ግጥሞች መካከል ለጥናቱ የተመረጡት ፳፫ ናቸው። ከእነዚኽ የቃል ግጥሞች ዐሥራ ሦስቱ በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ላይ የተዜሙ ወይም እሳቸውን በአሉታዊነት ይገልጻሉ። ዐሥሩ ደግሞ ለዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የተዜሙ ወይም እሳቸውን በአዎንታዊነት የሚገልጹ ናቸው። ይኹን እንጂ በዚኽ ጥናት ርእስ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን በአሉታዊነት የሚገልጹትን የቃል ግጥሞች ብቻ እንዲገልጽ ተደርጓል። ይኽ የተደረገው የጥናት ርእሱ በአሉታዊነትም፣ በአዎንታዊነትም የሚገልጹትን የቃል ግጥሞች በርኡሱ ማመልከት ባለመቻሉ ነው። የቃል ግጥሞቹ የተመረጡት በምቹ የናሙና አወሳሰድ ዘዴ (ኾን ተብሎ) ነው። የቃል ግጥሞቹ ልውጠት እና ቅጥለት የተመረመረውና የተተነተነው በማነጻጸር ነው። በንጽጽሩም በቃል ግጥሞቹ የሚታዩትን የምእላዶች እና የቃላት አጠቃቀም ለውጦች፣ የሐረግ የሥንኝ አደራደር በአጠቃላይ ቅርጻቸው እና ይዘታቸው እንዲኹም የቃል ግጥሞቹ የተዜሙበት ቦታ፣ ጊዜ እና ያዜማቸው ሰው ማንነት ተመርምረዋል፤ ተተንትነዋል። በቃል ግጥሞቹ የተላለፉት ይዘቶች የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን ታሪክ ማንፀባረቃቸውን ወይም አለማንፀባረቃቸውን ለማረጋገጥ የተለያዩ የታሪክ ሰነዶች ለምሳሌ፣ የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ዜና መዋዕሎች፣ የገብረ ሥላሴ (፲፱፻፶፬)፣ የመርዕድ (1990)፣ የባሕሩ (፪ሺህ)፣ የሥርግው ሐብለ ሥላሴ (2002)፣ የሥርግው ገላው (2008)፣ የክራሚ (Crummey) (1971, 1969), የሮቢንሰን (Rubenson) (1966) ሥራዎች በማመሳከሪያነት ተፈትሸዋል። በቃል ግጥሞች የተነገረው ይዘት በጽሑፍ ከተመዘገበው የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ታሪክ ጋር ተመሳሳይ ወይም የተለየ መኾኑን በንጽጽር ለማረጋገጥ ተችሏል።

1.3) ንድፈሐሳባዊ ቀመር

ለዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የተዜሙ እና የተመዘገቡ የቃል ግጥሞች ልውጠታቸውን እና ቅጥለታቸውን ለመተንተን የሚረዳ ንድፈ ሐሳብ መጥቀስ አልተቻለም። ምክንያቱም በሥነቃል ጥናት እና ምርምር ንድፈ ሐሳቦች የሚያገለግሉት በአንድ አጋጣሚ ላይ ከዋኝ እና ተሳታፊዎች (audiences) ፊት ለፊት ተገናኝተው የቃል ግጥምን ሲያዜሙ ወይም ሲደረድሩ የሚፈጠር ልውጠትን ለመመርመር እና ለመተንተን ነው። ይኽ ጥናት ትኩረት ያደረገው በተለያዩ ጸሓፍት ሥራዎች ተመዝግበው በሚገኙ የቃል ግጥሞች ላይ በመኾኑ የልውጠታቸውን ንድፈ ሐሳባዊ ምክንያት መስጠት እና መተንተን አልተቻለም። ይኹን እንጂ፣ የቃል ግጥሞቹን ልውጠት ጸሓፍቱ

ከመመዝገባቸው በፊት ከዋኝ እና ተሳታፊዎች ፊት ለፊት ተገናኝተው በሚከውኑበት ኺደት ወይም በንግግር መካከል የቃል ግጥሞቹ በመጠቀሳቸው ምክንያት ሊኾን ይችላል የሚል ንድፈ ሐሳባዊ መላምት መስጠት ይቻላል። ይኸም የቃል ግጥሞቹ ልውጠት በቃል ተደርሰው ተሳታፊዎች በተገኙባቸው የተለያዩ አጋጣሚዎች እየተከወኑ ወይም እየተነገሩ ከትውልድ ወደ ትውልድ ወይም ከአንዱ ወደ ሌላው በቃል ሲተላለፉ ሊኾን ይችላል የሚል ንድፈሐሳባዊ መላምት ላይ በመመሥረት ስለ ለውጡ ትንተና መስጠት ይቻላል። ሌላው መላምት ልውጠቱ የተፈጠረው ጸሓፍቱ ሲከወኑ የሰሟቸውን የቃል ግጥሞች በትክክል ለመመዝገብ ባለመቻላቸው ሊኾን ይችላል። ሲዜሙ የሰሟቸውን የቃል ግጥሞች ወዲያውኑ በጽሑፍ ወይም በቴክኖሎጂ ውጤቶች በመታገዝ ጸሓፍቱ ለመመዝገብ እንደ ማይችሉ የማኅበረሰባችን የዕድገት ደረጃ ምስክር ነው። የቃል ግጥሞቹ ሲዜሙ እንደ ተሰሙ ኾነው ለመመዝገብ የሚችሉበት የቴክኖሎጂ ዐቅም አለመኖር ለልውጠታቸው ምክንያት ይኾናል ተብሎ ይታመናል። እነዚኽን ንድፈሐሳባዊ መላምቶች መሠረት በማድረግ ጥቆማ ከመስጠት ያለፈ ትንተና መስጠት ያስቸግራል።

ከዚኽ በላይ የተገለጹት ንድፈሐሳባዊ መላምቶች እንደተጠበቁ ኾነው በዚኽ ጥናት ትኩረት የተደረገባቸው የቃል ግጥሞች አንዳንዶቹ ተለውጠው መተላለፋቸው የቀጠለው፣ ከተጻፉ ምንጮች በትክክል መገልበጥ ባለመቻሉ ነው። ከጥናቱ መገንዘብ እንደ ተቻለው፣ አንድን የቃል ግጥም ከተመሳሳይ ምንጭ የገለበጡ ጸሓፍት አንደኛው እንደ ተመዘገበው አድርጎ በትክክል ሲገለብጥ፣ ሌላኛው ሥንኝ ጨምሮ ወይም ቀንሶ (ቃል ቀንሶ ወይም ጨምሮ) በመገልበጡ ምክንያት ልውጠት ይፈጠራል። እንደዚሁም፣ አንድ ጸሓፊ በሌላ ሰው ሥራ ወይም በራሱ ሥራ ቀድሞ የተመዘገበን የቃል ግጥም ሲጠቅስ ስሕተት በመሥራቱ ምክንያት ልውጠት ተከስቷል። ልውጠቱ የቅርጽ ብቻ ወይም የቅርጽም፣ የይዘትም ሊኾን ይችላል። ተለውጠው በጽሑፍ የተመዘገቡ የቃል ግጥሞችም ለአንባቢው የተላለፉት እንዳልተለወጡ ተደርጎ ነው። ተለውጠው የተመዘገቡትን እና ለአንባቢ እንዲተላለፉ የተደረጉትን የቃል ግጥሞች ቀጥለው በሚቀርቡት ንዑስ ርእሶች ተተንትነዋል። በቅድሚያ የቅርጽ ልውጠት ብቻ የሚታይባቸውን የቃል ግጥሞች ቀጥለን እንመለከታለን።

2) የቅርጽ ልውጠት ብቻ የሚታይባቸው የቃል ግጥሞች

ለዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ በተዜሙት እና በጽሑፍ የተመዘገቡት የቃል ግጥሞች አንዳንዶቹ የቅርጽ ልውጠት ብቻ ይታይባቸዋል። የቅርጽ ልውጠት ከሚታይባቸው መካከል ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን በተለያዩ ስሞች በመጥራት የተመዘገቡት የሚከተሉት የቃል ግጥሞች ይጠቀሳሉ።

፩) ታጠቅን ባል ብሎ ማን አምኖ ይቆርባል፤
ሴሰኛውን ኀበዝ ያራቱን ማእዘን ባል
(ማኅተመ ሥላሴ፣ ፲፱፻፷፩፤ ፻፶፫)።

፪) ቴዎድሮስን ባል ብሎ ማን አምኖ ይቆርባል፤
ሴሰኛውን ኀበዝ ያራቱን ማእዘን ባል
(ሥርግው ሐብለ ሥላሴ፤ 2002፤ 151)።

በተራ ቁጥር ፩ እና ፪ በተጠቀሱት የቃል ግጥም የሚነበቡት መጠሪያዎች የወጡት በተለያዩ ጊዜያት ነው። "ታጠቅ" የሚለው ስም መጀመሪያ የተነገረው ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ተብለው ከመንገሣቸው በፊት ለዐቅመ ንጉሥነት ሳይበቁ ልጅ ካሣ እየተባሉ ይጠሩ በነበረበት ጊዜ ነው። ቃሉ መጀመሪያ ታስቦበት ሳይኾን ድንገት ለዐመፅ መቀስቀሻ የተነገረ ነው። የተነገረበት ታሪካዊ ምክንያትም፡- ልጅ

ካሣ "ወይዘሮ ተዋበችን አግብተው አማች ሆነው ሲኖሩ መድኃኒት ቀምሰው እራቴን ብለው ቢልኩ ወርች ሥጋ መጣልዎ። ልጅ ካሳም ወርች ሥጋስ አልበላም ገምቦኛም አይደለሁ ብለው መለሱ። ወይዘሮ ተዋበችም ሚስትዎ አገር ያ[የ]ለህምን[?] ታጠቅ እንሂድ ቢሉ ምነው የለኝ ብለው ይዘዋቸው ቋራ ወረዱ አባ ታጠቅ ተባሉ" በማለት ዊዳሌም (1897፤ 2) ይገልጹታል (ትኩረት የተጨመረ)። መርዕድም (1990፤ 85) ካሳ እና ተዋበች ከተጋቡ በኋላ ሚስትየዋ ባላቸው እንዲሸፍቱ ሲፈልጉ፤ "አገር የለህምን፣ ታጠቅ እንሂድ ብለዋቸው ነበር" በማለት ገልጸዋል። በዊዳሌም፣ በመርዕድም እንደተገለጸው "ታጠቅ" የሚለው ቃል መጀመሪያ የተነገረበት ዐውድ ልጅ ካሣ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚዊ ደረጃቸው ዝቅተኛ በነበረበት ጊዜ የተፈጸመባቸውን ክብረነክ ድርጊት እንዲቃወሙ፣ የንቀት ተግባር በፈጸሙባቸው ወ/ሮ መነን ላይ የዐመፅ ተግባር እንዲፈጽሙ፣ ያላቸውን የጦር መሣሪያ ይዘው እንዲሸፍቱ ለመገፋፋት፣ ለመቀስቀስ ነበር። "ታጠቅ" የሚለውን ትዕዛዝ አመልካች ቃል በቋራ በርሓ ሽፍተው በነበረበት ጊዜ የተጠሩበት (የተጠቀሙበት) ስለመኾኑ ማስረጃ ማግኘት አልተቻለም። ድንገት እሳውን ለመቀስቀስ የተነገረው ቃል ጠባያቸውን ይገልጻል ተብሎ በመታመኑ ከነገሡ በኋላ "አባ" የሚል ቃል ታክሎበት "አባ ታጠቅ" በማለት የፈረስ ስማቸው ኾነ። "አባ" የሚለው ቃልም የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን ጀግንነት ይገልጻል ከተባለው "ታጠቅ" ከሚለው የፈረስ ስማቸው ጋር ተጣምሮ በቅፅል ስምነት እሳቸውን ለመጥራት አገልግሏል። ቃሉ መጀመሪያ በመቀስቀሻነት፣ ሲነግሡ በፈረስ ስምነት፣ በተራ ቁጥር ፩ በተጠቀሰው የቃል ግጥሙ ዐውድ ደግሞ በመጠሪነት አገልግሏል። "አባ ታጠቅ" (የታጠቅ ጌታ) የሚለው የፈረስ ስማቸው ውስጠ ምስጢር ጠላቶችህን "ቸል ሳትል፣ ሳትዘነጋ፣ ጊዜ ሳትሰጥ ተዘጋጅተህ ጠብቃቸው" ማለት ነው በማለት ማኅተመ ሥላሴ (1969፤ 205) ይገልጻሉ።

በተራ ቁጥር ፪ የተጠቀሰው የቃል ግጥም የሚነበበው ቴዎድሮስ በሚለው የንግሥና መጠሪያ የተጠሩት ልጅ (በኋላ ደጃዝማች) ካሣ ብዙዎቹን መሳፍንት አሸንፈው የበላይነታቸውን ካረጋገጡ በኋላ ነው። ደጃዝማች ካሣ ራስ ዐሊን አይሻል ላይ ድል ካደረጉ በኋላ ለመንገሥ በቅርብ ርቀት በነበሩት በደጃዝማች ውቤ ላይ ዘመቱ። ደጃዝማች ውቤን ለመውጋት ጦራቸውን ሲያበረታቱ፣ "ስሜን ስሜን እነግርሀአለሁ ያልሁህ ወታደር ስሜም ቴዎድሮስ ነው አሉ" (ሊትማን፣ ፲፱፻፪፤ ፲፰)። ከዚኽም መገንዘብ የሚቻለው "ቴዎድሮስ" የሚለውን የንግሥና ስማቸውን ለሕዝባቸው ያስተዋወቁት ከመንገሣቸው ከቀናት በፊት መኾኑን ነው። ደጃዝማች ውቤን ድል ካደረጉ በኋላ የካቲት ዐምስት ቀን ፲፰፻፵፯ ዓ. ም. ደረስጌ ላይ ሲነግሡ በዚኹ ስማቸው ተጠሩ። "ቴዎድሮስ" በሚለው መጠሪያቸው ለማሞገስ አዝማሪ ያዜመው የቃል ግጥም ወደ ሸዋ ዘምተው ግብር ባገቡበት ዕለት መኾኑን ሥርግው ሐብለ ሥላሴ (2000) ገልጸዋል።

ከተጠቀሱት ኹለት የቃል ግጥሞች አንደኛው "ታጠቅ" የሚለው የፈረስ ስም፣ ኹለተኛው ደግሞ "ቴዎድሮስ" የሚለው የንግሥና ስም መጠቀሳቸው በቃል ግጥሙ ይዘት ላይ ልውጠት

አላስከተለም። የኹለቱም የቃል ግጥሞች ሠም በየቦታው ቁባት የሚቆብቱትን፣ ዘማዊውን "ታጠቅ" ን/ "ቴዎድሮስ" ን ባንድ ሴት ይረጋሉ፣ ይወሰናሉ ብሎ በማመን ለመቁረብ የሚወስን የለም የሚል ነው። ወርቁ ደግሞ ምኞታቸው ታላቅ የኾነውንና መንግሥታቸውን ለማስፋፋት የተነሡት ጀግናውን ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ባንድ አቅጣጫ በሚገኝ ክፍለ ግዛት አይወሰኑም፤ በኹሉም አቅጣጫዎች የሚገኙ ክፍለ ግዛቶችን ጠቅልለው በመያዝ ለመግዛት ይፈልጋሉ ማለት ነው። በቃል ግጥሞቹ የተፈጠረው ልውጠት ንጉሡ በፈረስ እና በንግሥና ስሞቻቸው መጠራታቸው ነው። "ታጠቅ" የሚለው ስም የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ፈረስ መጠሪያ ቢኾንም የእሳቸውን ጀግንነትና ቅልጥፍና ይገልጻል፤ ያሞግሳል። ጀግንነታቸውን በሚገልጸውና በሚያሞግሰው የፈረስ ስማቸው መጠራታቸውም ደስ ያሰኛቸዋል እንጂ አያስከፋቸውም። ምክንያቱም በፈረስ ስም መጠራት የተለመደ ፈሊጥ ስለ ነበር ነው (ማኅተመ ሥላሴ፣ 1969፤ 203)። ማኅተመ ሥላሴ አክለው እንደገለጹት በጦርነትም፣ በሰላምም ጊዜ በአዝማሪ እና ግጥም በሚደረድሩ ሰዎች በፈረስ ስም መሞገስ የተለመደ ቢኾንም የዘወትር መጠሪያ አድርጎ መጠቀም ግን ትክክል ተደርጎ አይቆጠርም። በተለያዩ አጋጣሚዎችም የፈረስን ስም እየጠሩ ራስን ማንቆለጳጰስ የተለመደ ተግባር ነበር። በማኅተመ ሥላሴ ከተገለጸው የፈረስ ስም አጠቃቀም መረዳት እንደሚቻለው ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን በፈረስ ስማቸው መጥራትና ማሞገስ ትክክለኛ ተግባር ነው። ስለዚኽም በተራ ቁጥር ፩ በተጠቀሰው የቃል ግጥም ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ በፈረስ ስማቸው መጠራታቸው ባህሉ የሚፈቅደውና እሳቸውም የሚመርጡት ነው። ባባታቸውና በናታቸው የወጣላቸውን "ካሣ" የሚለውን መጠሪያ "ቴዎድሮስ" በሚለው የንግሥና ስማቸው የተኩት ራሳቸው ወደውና ፈቅደው እንደነበር ቀደም ሲል ተገልጿል። "ቴዎድሮስ" የሚለውን መጠሪያ ለራሳቸው ማውጣታቸውን ያሳወቁት መንገሣቸውን ለሠራዊታቸው በነገሩበት ዕለት ነው። ራሳቸው መርጠው ለራሳቸው ባወጡት ቴዎድሮስ በሚለው የንግሥና ስም መጠራታቸውን፣ መሞገሳቸውን ቢወዱት እንጂ አይጠሉትም። ንጉሡን "ቴዎድሮስ" ወይም "ታጠቅ" በማለት በኹለቱም ስሞች መጥራትም ክብራቸውን አይቀንሰውም። ከዚኽም በተጠቀሱት የቃል ግጥሞች አንደኛውን መጠሪያ በሌላኛው ተክቶ ንጉሡን በመጥራት የታየው ልውጠት የቅርጽ ብቻ ነው ማለት ይቻላል።

በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ላይ የተዜሙት የቃል ግጥሞች የቃልም፣ የምእላድም ልውጠት ይታይባቸዋል። ይኽንንም ቀጥለው በተጠቀሱት ሦስት የቃል ግጥሞች እንመለከታለን።

፩) አንጥረኛ ብዙ የንጉሡ ቤት
ባል ዐልቦ አደረጉት ይኽን ኹሉ ሴት
(ዊዳሌ፣ ፲፱፻፺፯፣ ፴፩)።

፪) አንጥረኛው ብዙ በቴዎድሮስ ቤት፣
ባላልቦ_አደረጉት ይኽን ኹሉ ሴት
(ኅሩይ ወልደ ሥላሴ፣ ፳፻፩፣ ፴፱)፤
ደስታ ተክለ ወልድ፣ ፲፱፻፷፪፣ ፻፫፤
ማኅተመ ሥላሴ፣ ፲፱፻፷፩፣ ፻፸፬)።

፫) አንጠረኛው ብዙ ከንጉሡ ቤት።
ባለዐልቦ አደረጉት ይኼን ኹሉ ሴት።
(ሥርግው ገላው፣ 2008፤ 232)።

የተጠቀሱት የቃል ግጥሞች በንጉሡ ቤት ብዙ አንጥረኞች መኖራቸውን ይገልጻሉ። አንጥረኞቹ የሚገኙበትን ቤት ለመግለጽ ሦስቱም የቃል ግጥሞች የተለያዩ ምእላዶችን ተጠቅመዋል። በተራ ቁጥር ፩ የተጠቀሰውን የቃል ግጥም የመዘገበው (ያዜመውም ሊኾን ይችላል) በመጀመሪያው ሥንኝ "የንጉሡ ቤት" በሚለው ኹለተኛው ሐረግ ብዙ አንጥረኞች የሚገኙበትን ቤት ለመግለጽ /የ/ የሚል ምእላድ ተጠቅሟል። ምእላዱ በሰዋስዋዊ አገልግሎቱ ባለገንዘብነትን፣ ባለቤትነትን፣ የንጉሡን የቤት ባለቤትነት ይገልጻል። በተራ ቁጥር ፪ በተጠቀሰው የቃል ግጥም በመጀመሪያው ሥንኝ "በቴዎድሮስ ቤት" በሚለው ኹለተኛው ሐረግ /በ/ የሚለው ምእላድ መገኛ ቦታን ስለሚያመለክት በቴዎድሮስ ቤት ብዙ አንጥረኞች መኖራቸውን ይገልጻል። በተራ ቁጥር ፫ በተጠቀሰው የቃል ግጥም በመጀመሪያው ሥንኝ ኹለተኛ ሐረግ "ከቴዎድሮስ ቤት" በሚለው ሐረግ /ከ/ መነሻ ምእላድን ይገልጻል። ይኹን እንጂ በተጠቀሰው የቃል ግጥም ዐውድ በተለምዶ የሚነገረውን ወይም በዘየ ንግግርነት መገኛ ቦታን ይገልጻል። በሦስቱም የቃል ግጥሞች ይዞታን/የ/፣ መገኛን /በ/ እና መነሻን /ከ/ የሚገልጹት ምእላዶች ቅርጽም፣ የትርጉምም ልውጠት አስከትለዋል። በቃል ግጥሞቹ የተነገረው ይዘት ግን አንድ ዓይነት ነው።

በተራ ቁጥር ፩ እና ፫ በተጠቀሱት የቃል ግጥሞች "ንጉሥ" ፣ በተራ ቁጥር ፪ በተጠቀሰው ደግሞ ቴዎድሮስ" የሚሉት መጠሪያዎች በቅደም ተከተል ይነበባሉ። "ንጉሥ" የሚለው መጠሪያ ዘውድ ጭኖ ዙፋን ላይ የተቀመጠ የሀገር መሪን ይጠራል። "ንጉሥ" በሚለው መጠሪያ ላይ የታከለው "ኡ" የሚለው አናባቢም የሚታወቀውን ወይም በቅርብ ርቀት ያለውን በዙፋን ላይ ኾኖ ሀገር የሚመራውን ወይም ይመራ የነበረውን ሰው ያመለክታል፤ ይገልጻል። ከቃል ግጥሙ ዐውድ መረዳት እንደሚቻለው "ኡ" የሚለው አናባቢ የሚያመለክተው ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን ነው። የቃል ግጥሙ ከተመዘገበበት ዐውድ መረዳት እንደሚቻለው "ንጉሥ" የሚለው መጠሪያ "ቴዎድሮስ" የሚለውን ስም ተክቶ የገባ ነው። በቃል ግጥሞቹ አንደኛው መጠሪያ ሌላኛውን ተክቶ መግባቱ በቃል ግጥሞቹ ይዘት ላይ ልዩነት (ልውጠት) አላስከተለም። ሦስቱም የቃል ግጥሞች በሠማቸውም፣ በወርቃቸውም ያስተላለፉት ይዘት ተመሳሳይ ነው። በሠማቸው ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ለኹሉም ሴቶች በእግራቸው ላይ የሚያስሩት አልቦ የሚባል ጌጥ ሸለሟቸው፣ ሰጧቸው ማለትን ይገልጻሉ። በወርቃቸው ደግሞ "ወንድ ወንዱን ገድለው ሴቱን ያለ ባል አስቀሩት" የሚል ይዘት ተላፍፎባቸዋል። ስለኾነም በቃል ግጥሞቹ "ንጉሥ" የሚለውን መጠሪያ ቴዎድሮስ" በሚለው ስም ተክቶ መጠቀም የቅርጽ እንጂ የይዘት ልውጠት አላስከተለም።

የቃል ግጥሞቹን የመዘገቡ ጸሓፍት የተዜሙባቸውን ምክንያቶች እና ቦታዎች የተለያዩ መኾናቸውን ገልጸዋል። አለቃ ወልደ ማርያም ዘምሁይ ከጻፉት እና ዊዳሌ (፲፱፻፺፯) ካሳተሙት የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ዜና መዋዕል መረዳት እንደሚቻለው በተራ ቁጥር ፩ የተጠቀሰው የቃል ግጥም የተዜመው ጎጃም ልዩ ስሙ እንጅባራ በተባለ ቦታ ነው። የቃል ግጥሙ የተዜመበት ምክንያትም፣ ተድላ ጓሉ

ለአገው ምድር ግራ አዝማች ዓለሜን ሹሞ ወታደር ተሠሪ[3] በማስገባቱ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ተቆጥተው "እንጃባራ" [እንጅባራ] ላይ ድንገት ጦርነት ይከፍቱበታል። በጦርነቱም ከባላገርም፣ ከወታደርም ከሞተው ሌላ ፳ሺህ ይማረካል። ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስም የተማረከውን አሰብስበው ባለ ወግ[4] ጠርተው በዕለቱም፣ በነጋታውም በጠበንጃ እና በጎራዴ ያስገድሏቸዋል። በድርጊቱ ያዘነች አንዲት ሴት የተጠቀሰውን የቃል ግጥም አንጎራጎረች (ዌዳሌ፣ ፲፰፻፶፪)። ሥርግው ገላው (2008፤ 231- 232) በበኩላቸው ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ከተድላ ጓሉ ጋር እንጅባራ ላይ ባደረጉት ውጊያ ከባላገርም፣ ከወታደርም ፳ ሽህ ተማረከ። ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ኹሉንም ምርኮኞች እንዲገደሉ በማድረጋቸው የጎጃም አልቃሽ በተራ ቁጥር ፫ የተጠቀሰውን የቃል ግጥም ማንጎራጎሯን ገልጸዋል።

ዌዳሌም፣ ሥርግው ገላውም ድርጊቱ የተፈጸመበትን ቦታ ቅጣቱ የተፈጸመባቸውን ሰዎች ብዛትና የለቅሶ ግጥሙን ያንጎራጎረችው ሴት መኾናን በተመሳሳይ ዘግበዋል። የኹለት ጸሓፍት ዘገባ መመሳሰል ምክንያት ቀድሞ ከቀረበው የዌዳሌ ዘገባ ላይ ሥርግው ገላው በመመሥረታቸው ይመስላል። በምርኮኞቹ ላይ ቅጣቱ የተፈጸመበትን ኹኔታ ዌዳሌ "አካላቸውን በመቁረጥ ተገደሉ" በማለት ሲገልጹ ሥርግው ገላው በበኩላቸው "በጥይት እና በጎራዴ" መገደላቸውን ገልለጸዋል። ይኽም በኹለቱ ጸሓፍት መካከል መጠነኛ ልዩነት መኖሩን ይገልጻል።

ጎሩይ (፳፻፩፤ ፹፰ - ፹፱) በበኩላቸው በተራ ቁጥር ፪ የተጠቀሰው የቃል ግጥም የተዜመበትን ምክንያት፣ ቦታውንና ያዜመችውን ሴት በተመለከተ የዘገቡት ከዌዳሌም፣ ከሥርግውም ይለያል። ጎሩይ እንደዘገቡት ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ጐንደር ከተማን አጥፍተው ወደ ደብረ ታቦር ይመለሳሉ። መመለሳቸውን የሰሙ ፷፻ የሚኾኑ ሰዎች "ጥቃት ያደርሱብናል" ብለው በመፍራት ወደ በረሓም፣ ወደ ዋሻም በመሸሸ ለማምለጥ ይሞክራሉ። በመሸሸ ላይ በነበሩት ሰዎች ላይ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ድንገት ስለደረሱባቸው አንዳንዶቹ በድንጋጤ ይሞታሉ፤ ሌሎቹ ደግሞ በፍርኻት ይርዳሉ። ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስም በፍርኻት የሚርዱትን ወንዶች ወታደሮቻቸው ይዘው እንዲገድሏቸው ያዛሉ። የታዘዙት ወታደሮችም ኹሉንም ወንዶች ገድለው ሴቶችን በቦታው ትተዋቸው ይኼዳሉ። በድርጊቱ ያዘነች አንዲት ሴትም በተራ ቁጥር ፪ የተጠቀሰውን የለቅሶ ግጥም አንጎራጎረች በማለት ጎሩይ ይገልጻሉ። ጎሩይም፣ ማኅተመ ሥላሴም (፲፱፻፳፩ ፤ ፻፸፬) እንደ ዘገቡት ድርጊቱ የተፈጸመበትን ቦታ፣ ቅጣቱ የተፈጸመባቸውን ሰዎች ብዛት እና የለቅሶ ግጥሙን ያንጎራጎረችው ሴት መኾናን በተመሳሳይ መንገድ ዘግበዋል።

ጎሩይ የተጠቀሰውን ድርጊት እና የቃል ግጥሙን የዘገቡት ለመጀመሪያ ጊዜ በ፲፱፻፲ ዓ. ም. ባሳተሙት መጽሐፍ ሲኾን ማኅተመ ሥላሴ ደግሞ በ፲፱፻፳፩ ዓ. ም. ባሳተሙት መጽሐፍ ነው።

[3] ተሠሪ የሚለው ቃል "በቀድሞው ጊዜ በገባር ቤት ተመድቦ፣ ተመርቶ የሚቀመጥ ወታደር" ማለትን ይገልጻል (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1993፤ 114)።

[4] ባለ ወግ የሚለው ቃል

:

ይኸም ማኅተመ ሥላሴ ዘገባቸውን ከማቅረባቸው በፊት የኅሩይን ዘገባ ተመልከትውት ሊኾን ይችላል የሚል ግምት እንዲፈጠር ያደርጋል።

እንደ ዌዳሌ ዘገባ የቃል ግጥሙ የተዜመው ጎጃም ውስጥ ልዩ ስሙ እንጅባራ በተባለ ቦታ ነው። የቃል ግጥሙ የተዜመውም ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ከተድላ ጓሉ ጋራ አብረው በወጓቸው ሰዎች ላይ በፈጸሙት ቅጣት ምክንያት ነው። በኅሩይ ዘገባ ደግሞ የቃል ግጥሙ የተዜመው በጎንደር እና በደብረ ታቦር ከተማዎች መካከል በሚገኝ ልዩ ስሙ ባልተገለጸ ቦታ ነው። የቃል ግጥሙ የተዜመውም የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን ቅጣት ፈርተው ወደ በረሓም፣ ወደ ዋሻም ይሸሹ በነበሩ ሰዎች ላይ በፈጸሙት ቅጣት ምክንያት ነው። ቅጣቱ የተፈጸመባቸው ሰዎች ጥፋት ምን እንደ ነበር አልተገለጸም። በኅሩይም ፣ በዌዳሌም እንደተዘገበው የቃል ግጥሙ የተዜመው ስማቸው ባልተገለጹ ሴቶች ነው። ድርጊቱ የተፈጸመበት ቦታ፣ ቅጣቱ የተፈጸመባቸው ሰዎች እና የቃል ግጥሞቹን አዜሙ የተባሉት ሴቶች የተለያዩ ናቸው። የቃል ግጥሞቹ በተዜሙበት ጊዜ፣ ቦታ እና ቅጣቱ በተፈጸመባቸው ሰዎች ብዛት ልውጠት ይታያል። በቃል ግጥሞቹ የተፈጠረው ልውጠትም የቅርጽ ብቻ ነው። የቅርጽ ልውጠት የታየባቸው የቃል ግጥሞች ይዘት አንድ ዓይነት ነው። ይዘቱም ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ፈጸሙት ከተባለው እና በታሪክ ሰነዶች ከተመዘገበው ጋራ ሲነጻጸር ተመሳሳይ ነው።

ከዚኽ በታች የተጠቀሱት የቃል ግጥሞቹም የተለያዩ የቅርጽ ልውጠቶች ይታዩባቸዋል፤ ይዘታቸው ግን አንድ ዓይነት ነው። የቅርጽ ልውጠቶቹን እና የይዘቱን አለመለወጥ ለማስረዳት በቅድሚያ የቃል ግጥሞ እንደሚከተለው ተጠቅሰዋል።

፩) በሸዋ፣ በትግሬ፣ በወሎ፣ በጎጃም፣ በላስታ ያላችሁ፣
አንድ እግር በርበሬ መንቀል አቅቷችሁ፣
አንድዶ ለብልቦ አቃጥሎ ይፍጃችሁ
(ኅሩይ ወልደ ሥላሴ፣ ፳፻፩፤ ፴፪)።

፪) በሸዋ በትግሬ የተቀመጣችሁ፣
በጎጃም በላስታ የተቀመጣችሁ፣
፩ ዛላ በርበሬ መንቀል ቸግሯችሁ፣
በሉ እንዲኽ ቆጥቁጦ ለብልቦ ይፍጃችሁ
(ሥርግው ገላው፣ 2008፤ 231)።

፫) አንድ እግር በርበሬ መንቀል አቅቷችሁ፣
እንደዚኽ አንድዶ ለብልቦ ይፍጃችሁ
(ተክለ ጻድቅ፣ ፲፱፻፹፩፤ 245)።

በሦስቱም ተራ ቁጥሮች የተጠቀሱት የቃል ግጥሞች የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ስም አልተጠራም። የቃል ግጥሞቹ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን በመቃወም የተዜሙ መኾናቸውን መረዳት የሚቻለው የተዘሙበት ታሪካዊ ዳራ ሲታወቅ ነው። የተዜሙበትን ታሪካዊ ዳራ ለማወቅ ደግሞ የቃል ግጥሞቹን የመዘገቡት ጸሓፍት የገለጹትን መመልከት አስፈላጊ ነው። ይኸንንም በተራ ቁጥር ፩ የተጠቀሰውን የቃል ግጥም ታሪካዊ ዳራ በማስቀደም እንመለከታለን።

በተራ ቁጥር ፩ የተጠቀሰው የቃል ግጥም በምን ምክንያት እና የት ቦታ እንደተዜመ ኅሩይ (፳፻፩፤ ፴፪) እንደሚከተላው ይገልጻሉ። ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ጎንደርን ለማጥፋት ይኼዳሉ። በዚኽ ጊዜ የሚበዛው የጐንደር ሰው ተሰብስቦ ወደ ጣና ባሕር በመኼድ በምጽራሐ ደሴት ይጠለላል። ዳግማዊ

ዐፄ ቴዎድሮስም ጐንደርን ዘርፈው ወደ ምጽራሐ ደሴት ይኼዳሉ። ወታደሮቻቸውንም በታንኳ ተሳፍረው በመኼድ በደሴቱ የተጠለሉትን ሰዎች እንዲይዙ ያዛሉ። ወታደሮቹም በደሴቱ የተጠለሉትን ሰዎች ይይዛሉ። ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ወደ ተያዙት ሰዎች በመኼድ ወንዱንም፣ ሴቱንም፣ ልጁንም፣ ሽማግሌውንም የጎንደር ነገሥታት በየጊዜያቸው በደሴቱ ባሠሯቸው ትልልቅ ቤቶች በማስገባት በእሳት እንዲያቃጥሏቸው ወታደሮቻቸውን ያዛሉ። ወታደሮቹም በታዘዙት መሠረት የንጉሡን ቅጣት ይፈጽማሉ። ከቃጠሎው ያመለጠት አንዲት ሴት በተራ ቁጥር ፩ የተጠቀሰውን የቃል ግጥም አንጎራጎረች።

ሥርግው ገላው (2008፤ 231) በበኩላቸው በተራ ቁጥር ፪ የተጠቀሰውን የቃል ግጥሙ ያዜመችው በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ "እናቱዋ፣ አባቱዋ፣ እኅቱዋ፣ ወንድሙዋ በእሳት ተቃጥለውባት የቈጫት፣ የነደዳት አበራሽ የምትባል ሴት" መኾኗን ገልጸዋል። ሥርግው ገላው የአበራሽን ቤተሰቦች ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ በእሳት ማቃጠላቸውን እንጂ ቅጣቱን የፈጸሙበትን ቦታ አልገለጹም። ተክለ ጻድቅም (፲፱፻፹፩፤ 245) በተራ ቁጥር ፫ የተጠቀሰውን የቃል ግጥም ያዜመችው በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ቅጣት ከተከፉ ሰዎች አንዷ ምንትዋብ የተባለች ገጣሚ መኾኗን ገልጸዋል። ይኹን እንጂ፣ ተክለ ጻድቅ የቃል ግጥሙን ያዜመችበትን ምክንያት የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን ቅጣት ምንነት እና የተፈጸመበትን ቦታ አልገለጹም።

በቃል ግጥሞቹ የተገለጸው ታሪካዊ ድርጊት፣ ድርጊቱ የተፈጸመበት ቦታ እና ኹኔታ እንዲኹም የቃል ግጥሞችን ያዜሙት ሰዎች ማንነት የተለያየ ነው። በተራ ቁጥር ፩ የተጠቀሰውን የቃል ግጥም የመዘገቡት ጎሩይ በቃል ግጥም የተገለጸው ቅጣት የተፈጸመበት ቦታ እና ኹኔታ በሥርግው ገላውም፣ በተክለ ጻድቅም ከተገለጸው ይለያል። ጎሩይ የቃል ግጥሙን ያዜመችውን ሴት በስም አለመግለጻቸው በሥርግው ገላውም፣ በተክለጻድቅም ከተገለጸው ይለያል። በሦስቱም ጸሓፍት እንደተገለጸው የቃል ግጥሞች የተዜሙት ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ በፈጸሙት ቅጣት ባዘኑ ሴቶች ነው።

በተራ ቁጥር ፩፣ ፪ እና ፫ የተጠቀሱት የቃል ግጥሞች ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ቅጣታቸው የበዛ፣ የከፋ እና የከበደ መኾኑን ይገልጻሉ። ጥፋተኛ ባሏቸው ሰዎች ላይ ይፈጽሙት የነበረው ከባድ ቅጣት የተገለጸው የማቃጠል ጠባይ ያለውን በርበሬ እና የበርበሬ ተክልን በለዋጭ ዘይቤነት በመጠቀም ነው። በለዋጭ ዘይቤውም በተራ ቁጥር ፩ እና ፫ የአንድ እግር በርበሬን፣ በተራ ቁጥር ፪ በተጠቀሰው የቃል ግጥም ደግሞ የአንድ ዛላ በርበሬን ጠባይ ወርሰዋል። ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የበርበሬን የመፋጀት፣ የማቃጠል እና የመለብለብ ጠባይ መውረሳቸው ድርጊታቸው ሰዎችን መጉዳቱን ይገልጻል። በርበሬ በተፈጥሮው የማቃጠል ባሕርይ ስለአለው ምርቱም፣ ዱቄቱም ምላስን፣ ዐይንን እና አፍንጫ ይቆጠቁጣል።

ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን ከሥልጣናቸው በኃይል ለማስወገድ የሸዋ፣ የትግሬ፣ የወሎ፣ የጎጃም እና የላስታ ነዋሪዎች አለመታገላቸው ድክመታቸው መኾኑን በተራ ቁጥር ፩ እና ፪ የተጠቀሱት የቃል ግጥሞች ይገልጻሉ። በተራ ቁጥር ፫ የተጠቀሰው የቃል ግጥም ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን ታግሎ ከሥልጣናቸው ካላስወገዱ ክፉ ቅጣታቸውን እንዲፈጽሙበት ቢመኝም በየትኞቹ ግዛቶቻቸው

የሚኖረው ሕዝብ ላይ እንደኾነ አልተገለጸም። ይኹን እንጂ፣ የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ግዛቶች በተራ ቁጥር ፩ በተጠቀሰው የቃል ግጥም የተገለጹት ስለነበሩ ክፉ ምኞቱ በእነሱ ላይ እንዲደርስ የተባለ ነው ማለት ይቻላል። በጽሑፍ ከተመዘገበው ታሪካቸው መረዳት እንደሚቻለው በቃል ግጥሞቹ በተጠቀሱት ቦታዎች የሚኖሩ ተተቀናቃኞቻቸው በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የሥልጣን ፍጻሜ ጠንካራ ተቃዋሚዎች ነበሩ። ተቃዋሚዎቹም በጎጃም ተድላ ጓሉ፣ በላስታ ዋግሹም ጎበዜ (በኋላ ዐፄ ተክለ ጊዮርጊስ ተብለው ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን የተኩት)፣ በሸዋ ሠይፉ ሣህለ ሥላሴ እና በዛብህ በወሎ ደግሞ ደጃዝማች ሊበን አህመዴ ነበሩ[5] (ባሕሩ፣ ፪ሺህ)።

ሦስቱም የቃል ግጥሞች የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን ከባድ እና የከፋ ቅጣት ለማስቀረት የሚቻለው እሳቸውን ከሥልጣን በማስወገድ መኾኑን ይገልጻሉ። በተለያዩ ግዛቶች የሚኖረውን ሕዝብ በመተባበር፣ በመረዳዳት፣ በርትቶ እና ጠንክሮ በመቃወም እና በመታገል ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን ከሥልጣናቸው ማስወገድ እንዳለበት ይቀሰቅሳሉ። በተጠቀሱት ቦታዎቸ የሚኖረው ሕዝብ ታግሎ ከሥልጣን አለማስወገዱን ደግሞ የራሱ ጥፋት ወይም ድክመት አድርገው ይቆጥራሉ። በሕዝቡ ድክመትም በጆሮ የሚሰማው፣ ሲተገብሩት የሚታየው እና የሚታወቀው ሰውን በእሳት "አንድደው"፣ "ለብልበው"፣ "አቃጥለው" እና "ቆጥቁጠው" "የመፍጀት" ቅጣታቸውን በእናንተም ላይ ይፈጽምባችሁ" በማለት ይመኛሉ፤ ይረግማሉ። የቃል ግጥሞቹ "የሚፈጸምባችሁ ቅጣት ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን ከሥልጣናቸው በኀይል ለማስወገድ ወኔ እና ድፍረት የማጣታችሁ ውጤት ነው፤ ይበላችሁ" በማለት ይረግማሉ። በተጠቀሱት ቦታዎች በሚኖረው ሕዝብ ላይ የእሳቸው ከባድ ቅጣት እንዲፈጽምበት መርገሙ በአካባቢው ያሉትን የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ተቃዋሚዎች እንዲያግዝ ወይም እንዲተባበር ለመቀስቀስ በማሰብ ይመስላል።

በቃል ግጥሞቹ በሸዋ፣ በትግራይ፣ በወሎ፣ በጎጃም እና በላስታ ነዋሪ ሕዝብ ላይ ከባድ ቅጣት ይፈጽሙበት የተባሉት ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ በለዋጭ ዘይቤ ተገልጸዋል። ለዋጭ ዘይቤውም በተራ ቁጥር ፩ እና ፫ በተጠቀሱት የቃል ግጥሞች የበርበሬ ተክል ሲኾን በተራ ቁጥር ፪ በተጠቀሰው የቃል ግጥም ደግሞ የበርበሬ ዛላ ነው።

በተራ ቁጥር ፪ በተጠቀሰው የቃል ግጥም ዘይቤውን ለመፍጠር "ዛላ" እና "መንቀል" የሚሉት ቃላት መቀናጀታቸው ትክክል አይደለም። ዛላ በርበሬ ይለቀማል እንጂ አይነቀልም። ስለዚኽ ትክክለኛው የቃላት ቅንጅት "አንድ እግር በርበሬ መንቀል አቅቷችኹ" በሚለው ሥንኝ የሚነበበው ነው። በበርበሬ ከመቃጠል እና ከመለብለብ ለመዳን የበርበሬ ዛላ የሚያፈራውን ተክሉን መንቀል እና ማስወገድ መፍትሔ ተደርጎ እንደተገለጸው ኹሉ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ በሕዝብ ላይ ከሚፈጽሙት ከባድ ቅጣት ለመዳን የግዛታቸው ሕዝብ ተባብሮ ከሥልጣናቸው ሊነቅላቸው ያስወግዷቸው እንደሚገባ በተጠቀሱት የቃል ግጥሞች ተገልጿል።

[5] በቃል ግጥሞቹ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ያስተዳድሯቸው የነበሩት የሰሜን፣ የወልቃይት፣ የደምቢያ እና የበጌምድር ነዋሪ ሕዝብ እሳቸውን ከሥልጣን የማስወገድ ኀላፊነት እንደ አለበት አይገለጽ እንጂ "በወልቃይት ጥሶ ጎበዜ የንጉሡን ሥልጣን እያዳካመ ይግረምህ ብሎ ጎንደር ከተማን ለመያዝ የበቃ" የተቃውሞ እንቅስቃሴ አድርጓል (ባሕሩ፣ ፪ሺህ፤ 42)።

በሦስቱም ተራ ቁጥሮች የተጠቀሱት የቃል ግጥሞች ተመሳሳይነትም፣ ልዩነትም ይታይባቸዋል። ተመሳሳይነታቸውም፣ አንደኛ፣ በሦስቱ ተራ ቁጥሮች የተጠቀሱት የቃል ግጥሞች ይዘት አንድ ዓይነት መኾኑ፣ ኹለተኛ፣ የቃል ግጥሞቹን የመዘገቡ ሰዎች እንደገለጹት የቃል ግጥሞቹ የተዜሙት ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ በፈጸሙት ቅጣት ስሜታቸው በተጎዱ ሰዎች ነው መባሉ፤ ሦስተኛ፣ በተራ ቁጥር ፪ በተጠቀሰው የቃል ግጥም ወሎ ካለመጠራቱ በስተቀር በተራ ቁጥር ፩ እና ፪ በተጠቀሱት የቃል ግጥሞች "ክፉ ይድረስባቸው" የተባሉት ሰዎች የሚኖሩባቸው ቦታዎች ተመሳሳይ መኾናቸው የሚሉት ናቸው።

ቀደም ሲል እንደተጠቆመው በቃል ግጥሞቹ መካከል ልዩነቶች ያታያሉ። ልዩነቶቹም፣ አንደኛ፣ ቅጣቱ የተፈጸመባቸው ሰዎች የተለያዩ ናቸው መባሉ፤ ኹለተኛ፣ የቃል ግጥቹን ያዜሙት ሰዎች የተለያዩ መኾናቸው፤ ሦስተኛ፣ የቃል ግጥሞቹ በተለያዩ ቦታዎች መዜማቸው፤ አራተኛ፣ በሦስቱም የቃል ግጥሞች የሥንኝ አደራደር፣ የሥንኝ ቁጥር መብዛት እና ማነስ መኖሩ፤ ዐምስተኛ፣ በተራ ቁጥር ፩ እና ፪ እንደተመለከተው በተራ ቁጥር ፫ በተጠቀሰው የቃል ግጥም ክፉ ምኞት የቀረበበት በየትኞቹ አካባቢዎች በሚኖረው ሕዝብ ላይ መኾኑ አለመገለጹ፤ ስድስተኛ፣ የቃል ግጥሞቹን የመዘገቧቸው ሰዎች ከሰጧቸው ገለጻዎች መረዳት እንደሚቻለው ለሦስቱም የቃል ግጥሞች መዜም የተሰጡት የታሪክ ዳራዎች ልዩነት የሚታይባቸው መኾኑ የሚሉት ናቸው። የቃል ግጥሞቹ ይዘት የቀረበው ተመሳሳይነት ያላቸውን ቃላት ለዋውጦ በመጠቀም ነው። ቃላትን ለውጦ መጠቀምም፣ በቃል ግጥሞቹ የሚታዩት ልዩነቶችም የይዘት ልውጠት አላስከተሉም። በቃል ግጥሞቹ የጣየው ልውጠት የቅርጽ ብቻ ነው።

እስከ ዐኹን በተመለከትናቸው የቃል ግጥሞች የቃል አጠቃቀም፣ የሥንኝ አደራደር ቦታ መቀያየር (መለዋወጥ)፣የሥንኝ ቁጥር መቀነስ እና መጨመር መኖሩን መረዳት ተችሏል። ይኸም በቃል ግጥሞቹ ላይ የቅርጽ ልውጠት አስከትሏል። ልውጠት የታየባቸው የቃል ግጥሞችም በየተመዘገቡባቸው ሥራዎች ለአናባቢ ይተላለፋሉ።

ከዚኽ በላይ ከተገለጸው ሌላ በአንዳንድ የቃል ግጥሞች የቅርጽም፣ የይዘትም ልውጠት ይታያል። ይኽ ዓይነቱ ልውጠት ከዚኽ በታች በቀረበው ንዑስ ርእስ ተመልክቷል።

3) የቅርጽም፣ የይዘትም ልውጠት የሚታይባቸው የቃል ግጥሞች

የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን ጠባይ ለመግለጽ ከተዜሙት የቃል ግጥሞች መካከል አንዳንዶቹ ሥንኞቻቸው ተቀንሰው የተወሰኑት የሥንኞቻቸው ቁጥር ተለውጠው በተለያዩ ጸሓፍት ሥራዎች ተመዝግበዋል። በአንዳንዶቹ ጸሓፍት ሥራዎች ሥንኞች ተሟልተው በተመዘገቡት የቃል ግጥሞች የተገለጸው ይዘት በሌሎቹ ደግሞ የሥንኞች ቁጥር በመቀነሱ ምክንያት በተሟላ መንገድ እንደማይገለጽ መረዳት ተችሏል። ቀጥለው የተጠቀሱት የቃል ግጥሞች የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን ጠባይና ድርጊት ለመግለጽ የተዜሙ ናቸው። ቀጥሎ በተራ ቁጥር ፩ እና ፫ የተጠቀሱት የቃል ግጥሞች ማስተላለፍ የተፈለገውን ይዘት በምሉእነት እንዳስተላለፉ በተራ ቁጥር ፪ እና ፬

የተጠቀሱት ደግሞ እንዳላስተላለፉ መገንዘብ ይቻላል። ዝርዝሩን የቃል ግጥሞችን በመጥቀስ ይመረመራሉ።

፩) ታንበሳ ተዝኖን ተሰይጣን ተመልአክ አምላክ የሠራዎ፣
ያንበሳውም ለታ አንዱንም በርግጫ አንዱንም በጡጫ ሲያሰኝዎ ዋለ፣
የዝኖኑም ለታ ጫካውን ውድማውን ሲያስጥስዎ ዋለ፣
የሰይጣኑም ለታ ስደደው ግደለው ሲያሰኝዎ ዋለ፣
የመልአኩም ለታ ርቦታል አጉርሱት በርዶታል አልብሱት ሲያሰኝዎ ዋለ
ቆንጥረው ቆንጥረው ሁሉን ያካበቱ፣
የመጨረሻው ለት መቅደላ አፋፉ ላይ ግስላ ሆኑና ታነቁና ሞቱ
(ዓለማየሁ፣ ፲፱፻፶፬፤ ፳፰)።

፪) ታንበሳ ተዝኖን ተሰይጣን ተመልአክ አምላክ የሠራዎ፣
ያንበሳውም ለታ አንዱንም በርግጫ አንዱንም በጡጫ ሲያሰኘዎ ዋለ፣
የዝኖንም ለታ ጫካውን ውድማውን ሲያስጥስዎ ዋለ፣
ቆንጥረው ቆንጥረው ሁሉን ያካበቱ፣
የመጨረሻው ለት መቅደላ አፋፉ ላይ ግስላ ሆኑና ታነቁና ሞቱ
(ዓለማየሁ፣ ፲፱፻፷፯፤ ፸፪)።

፫) ከአንበሳ ከዝኖን፣ ከሰይጣን ከመላክ፣ አምላክ የሠራዎት (2)
ያንበሳውም ለታ፣ በጡጫ በርግጫ ሲያሰኝዎት ዋለ፣
የዝኖኑም ለታ፣ ጫካ ውድማውን ሲያስጥስዎት ዋለ፣
የሰይጣኑም ለታ፣ በርዶታል አልብሱት ሲያሰኝዎት ዋለ፣
የሰይጣኑም ለታ፣ ስደደው ግደለው ሲያሰኝዎት ዋለ፣
የመላኩም ለታ፣ በርዶታል አልብሱት ርቦታል አጉርሱት ሲያሰኝዎት ዋለ፣
ቆንጥረው ቆንጥረው፣ ኹሉን ያካበቱ፣
መቅደላ አፋፉ ላይ፣ ራስዎን ገለው ሞቱ።
(ዓለሙ ኢጋ በሲዲ ካሳተሙት የተወሰደ)

፬) ቆንጥረው ቆንጥረው ሁሉን ያካበቱ፤
የመጨረሻው ለት መቅደላ አፋፉ ላይ ግስላ ሆኑና ታነቁና ሞቱ
(ሥርግው ሐብለ ሥላሴ፣ 2000፤ 462)።

በተራ ቁጥር ፩ እና ፪ የተጠቀሱት የቃል ግጥሞች ከዓለማየሁ የተለያዩ ሥራዎች የተወሰዱ ናቸው። ዓለማየሁ በ፲፱፻፶፬ ዓ. ም. ባሳተሙት የመጀመሪያው መጽሐፋቸው የመዘገቡት የቃል ግጥም ሰባት ሥንኞች ሲኖሩት ከዐሥራ ሦስት ዓመት በኋላ በ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. ባሳተሙት ሌላኛው መጽሐፋቸው የመዘገቡት ደግሞ ዐምስት ሥንኞች አሉት። በመጀመሪያው መጽሐፋቸው ከመዘገቡት የቃል ግጥም በሌላኛው መጽሐፋቸው ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የሰይጣን እና የመልአክ ጠባዮች እየተፈራረቁ

እንደሚነግሡባቸው የሚገልጹት ኹለት ሥንኞች ተገድፈዋል። ይኽም በተራ ቁጥር ፩ በተጠቀሰው የቃል ግጥም የተገለጸው ይዘት በተራ ቁጥር ፪ በተጠቀሰው የቃል ግጥም ሙሉው እንዳይተላለፍ አድርጓል። በተራ ቁጥር ፩ ከተጠቀሰው የቃል ግጥም የሚነበቡት ሥንኞች ሦስት እና አራት በተራ ቁጥር ፪ በተጠቀሰው አለመመዝገባቸው የቅርጽም፣የይዘትም ልውጠት አስከትለዋል። የቅርጽ ልውጠቱ የሥንኞቹ መገደፍ ሲኾን የይዘት ልውጡ ደግሞ ክፉነት እና ደግነት የሚሉት ተቃራኒ ጠባዮች የጠቅላላ ጠባያቸው አካላት መኾናቸው አለመገለጻቸው ነው።

ዓለማየሁ በሌላኛው መጽሐፋቸው ኹለት ሥንኞችን ያልመዘገቡበትን ምክንያት እርግጠኛ ኾኖ መናገር ያስቸግራል። ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የሰይጣንም፣ የመልአክም ጠባዮች እንዳሏቸው የሚገልጹትን ሥንኝ አራትን እና ሥንኝ ዐምስትን በኹለተኛው መጽሐፋቸው አለመመዝገባቸው በራሳቸው መጽሐፍ ቀድመው የመዘገቡትን የቃል ግጥም በትክክል አለመቅዳታቸውን ያስረዳል። ይኽም በቃል ግጥሙ ለማስተላለፍ የተፈለገው ይዘት በምሉእነት እንዳይተላለፍ አድርጎታል።

በተራ ቁጥር ፫ የተዜመው የቃል ግጥም በዓለማየሁ በተመዘገበው እና በተራ ቁጥር ፩ በተጠቀሰው ጋራ በተመሳሳይ የዐፄ ቴዎድሮስን ጠባዮች የሚገልጹ ሥንኞች ተዚመዋል። በተራ ቁጥር ፫ የተጠቀሰው "የሰይጣኑም ለታ፣ በርዶታል አልብሱት ሲያስኝዎት ዋለ" በሚለው ሥንኝ ለሰይጣን በጎ ጠባይ ሰጥተው ያዜሙት በስሕተት ይመስላል። ስሕተቱንም ቀጥሎ ያለውን የሰይጣን ክፉ ጠባይ የተገለጸበትን ሥንኝ በማዜም አስተካክለውታል። በስሕተት ከተዜመው ሥንኝ ሌላ በተራ ቁጥር ፫ እና በተራ ቁጥር ፩ በተጠቀሱት የቃል ግጥሞች መካከል የምእላድ፣ የቃላት አጠቃቀም እና አቀማመጥ፣ የሐረግ እና የሥንኝ አደራደር ልዩነት ወይም ልውጠት ይስተዋልበታል። ከልዩነቶቹ ጥቂቶቹ በሚከተለው ሰንጠረዥ ቀርበዋል።

በዓለማየሁ የተመዘገበው	በዓለሙ የተዜመው	ልዩነት	የልዩነቱ መጠሪያ
ታንበሳ ተዥኖን ተሰይጣን ተመልአክ	ከአንበሳ ከዥኖን ከሰይጣን ከመልአክ	ተ እና ከ	ምእላድ
የሠራዎ	የሠራዎት	ት	ምእላድ
አንዱንም በርግጫ አንዱንም በጡጫ	በጡጫ በርግጫ	አንዱንም	የቃል/ሐረግ
ሲያሰኝዎ	ሲያሰኝዎት	ት	ምእላድ
ሲያስጥስዎ	ሲያስጥስዎት	ት	ምእላድ
ርቦታል አጉርሱት በርዶታል አልብሱት	በርዶታል አልብሱት ርቦታል አጉርሱት	ቃላት	አወቃቀር
የመጨረሻው ለት መቅደላ አፋፉ ላይ ግስላ ሆኑና ታነቁና ሞቱ።	መቅደላ አፋፉ ላይ፣ ራስዎን ገለው ሞቱ።	የቃላት	የሐረግ

በሥርግው ሐብለ ሥላሴ ተመዝግቦ የተገኘው እና በተራ ቁጥር ፬ የተጠቀሰው የቃል ግጥም በዓለማየሁም፣ በዓለሙም ከተመዘገቡት የቃል ግጥሞች በቅርጽም፣ በይዘትም ይለያል። የቅርጽ ልዩነቱ የተፈጠረው ሥርግው ሐብለ ሥላሴ በተጠቀሱት ሰዎች የተመዘገቡትን የቃል ግጥሞች

ሥንኞች ኹሉንም አለመመዝገባቸው ነው። የይዘት ልዩነቱም በሥርገው ሐብለ ሥላሴ ባልተመዘገቡት ሥንኞች የተገለጹት የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ጠባዮች አለመነገራቸው ነው። በዓለማየሁም፣ በዓለሙም የተመዘገቡት የቃል ግጥሞች ኹሉም ሥንኞች በሥርግው ሐብለ ሥላሴ ያልተመዘገቡት በትክክል ማስታዎስ ባለመቻሉ ወይም ኾን ብሎ በማሻሻል ሊኾን ይችላል።

በተራ ቁጥር ፩ እና ፫ በተጠቀሱት የቃል ግጥሞች ከተገለጸው መገንዘብ እንደሚቻለው ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ በጠባያቸው ተለዋዋጭነት የሚታዩባቸው ነበሩ። የሚፈራረቁባቸው ጠባዮችም ደግነት/ሩኅሩኅነት፣ ኃይለኝነት/ እልኸኛነት፣ ደፋርነት/ጀግንነት፣ ጨካኝነት ነበሩ። በሦስቱም ተራ ቁጥሮች ከተጠቀሱት የቃል ግጥሞች መረዳት እንደሚቻለው ከሚፈራረቁባቸው ጠባዮች መካከል ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን ለሞት የዳረጋቸው እልኸኛነታቸው እና ኃይለኛነታቸው ነው።

በተራ ቁጥር ፩ እና ፫ የተጠቀሱት የቃል ግጥሞች ሰባት ሥንኞች አሏቸው (በተራ ቁጥር ፫ የተመዘገበው የቃል ግጥም ዐምስተኛው ሥንኝ ሳይቆጠር)። በቃል ግጥሞቹ እንደተገለጸው የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን ጠባይ አምላክ ከአራት ጠባዮች መሥራቱን የቃል ግጥሞቹ ይገልጻሉ። የአንበሳ፣ የዝኆን፣ የሰይጣን እና የመልአክ ጠባዮች በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ላይ የሚነግሡት ተባብረው፣ ተጣምረው እና አንድ ኾነው ሳይኾን በየተራ እየተፈራረቁ ነው። ከቃል ግጥሞቹ መረዳት እንደሚቻለው ከተጠቀሱት ጠባዮቻቸው አንደኛው ሲነግሥባቸው (ጎልቶ ሲወጣ) ሌሎቹ ይሸረጣሉ (ይደበቃሉ)።

በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ላይ ከሚነግሡባቸው ጠባዮች ኹለቱ አንበሳ እና ዝኆን በገሀዱ ዓለም የሚታዩ እና ጠባዮቻቸውም የሚታወቁ ናቸው። የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ “የአንበሳ እና የዝኆን ጠባይ ይነግሱባቸዋል” መባሉ “ሰው በሥጋው ከእንስሳት አንድነት ያለው ፍጥረት ነው” ከሚለው አስተሳሰብ ጋራ ይመሳሰላል (ደስታ፣ ፲፱፻፷፪ ፤ ፲፬፻፷፯)። በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ይነግሟሉ የተባሉት ሰይጣን እና መልአክ መኖራቸው በእምነት ተቀባይነት ያላቸው ሰማያዊ ፍጡራን ናቸው። “የመልአክ ጠባይ ይነግሥባቸዋል” የሚለው አገላለጽ “ሰው በነፍሱ ከመልአክት አንድነት አለው” (ደስታ፣ ፲፱፻፷፪ ፤ ፲፬፻፷፯) ከሚለው ጋራ ይመሳሰላል። በአጠቃላይ የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ጠባይ ከአራት ባሕርያት እንደ ተመሠረተ የተገለጸው፣ በምድር ያለ ፍጥረት ኹሉ ሥር [መሠረት ማይ [ውሃ]፣ መሬት፣ ነፋስ፣ እሳት ናቸው። እሊህ [እኒኽ] አራቱ ባሕርያትም፣ ጠባያትም ይባላሉ … ጠባይም መገኛ፣ ማስገኛ ስለኾነ፣ የአካል ፣ የስም፣ የህላዌ ጥንት የሥራ ምንጭ የግብር መሠረት ይባላል” (ኪዳነ ወልድ፣ ፲፱፻፵፰፤ ፪፻፷፪) ከሚለው ጋራ ይመሳሰላል። እነዚኽ በኪዳነ ወልድ ከተጠቀሱት አራቱ ጠባዮች አንዱ ከሌላው የሚስማማ በመኾኑ በመካከላቸው ተቃርኖ የለም። እያንዳንዱ የምድር ፍጥረት የየራሱ ጠባይ እንዲኖረውም አድርገዋል። ነገር ግን በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ላይ የሚነግሡት የእንስሳት (አንበሳ እና ዝኆን) ጠባዮች ግንኙነታቸው በአሸናፊነት እና ተሸናፊነት ላይ የተመሠረተ ነው። ሰማያዊ የኾኑት የሰይጣን እና የመልአክ ጠባያትም በመካከላቸው ያለው ግንኙነት ቋሚ ጠላትነት ነው።

“አንበሳ የልበ ሙሉ፣ የደፋር፣ የአሸናፊ፣ የዝግና፣ የሐርበኛ፣ የንጉሥ ምሳሌ” (ደስታ፣ ፲፱፻፷፪፤ ፻፲፫) ተደርጎ ይቈጠራል። ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የአንበሳ ጠባይ በላያቸው ላይ ሲነግሥባቸው የልበ ሙሉነት፣ የደፋርነት፣ የአሸናፊነት እና የጀግንነት ተግባር ይፈጽማሉ ማለትን የቃል ግጥሙ ይገልጻል። ይኸው ጠባይ ሲነግሥባቸውም፣ ጠላቶቻቸውን እና ተቀናቃኞቻቸውን ያዘው” ፤ “እሰረው” ፤ “በለው” ፤ “ጣለው” ፤ “ግረፈው” ፤ “እጅና እግሩን ቁረጠው” ፤ በማለት በኀይል እና በጉልበት የበላይነታቸውን ያሰፍናሉ። የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች የሚፈቱት በጡጫ እና በርግጫ ነው፤ ከሚቀናቀኗቸው ሰዎች ጋራ የሚኖራቸውን ግንኙነት በአሸናፊነት እና በተሸናፊነት ላይ የተመሠረተ ነው። ይኸ ጠባያቸው የሥልጣን ተቀናቃኞቻቸውን እና ከአመራራቸው ያፈነገጡትን በዘዴ፣ በትዕግሥት፣ በብልኀት ፣ በትክክለኛ የዳኝነት እና የአስተዳደር ሥርዓት አለመምራታቸውን፤ የማይመረጠውን እና “ተገቢ አይደለም” የሚባለውን የኃይል መንገድ መከተላቸውን፣ በሕግ፣ በፍትሕ አለመመራታቸውን ይገልጻል። አንበሳ የአሸናፊነት፣ የጀግንነት ተምሳሌት እንደኾነው ኹሉ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስም በዘመናቸው ከሽፍትነት እስከ ንጉሥነት የተጓዙበት መንገድ በአሸናፊነት መኾኑን ያስረዳል። በሀገር ውስጥ ተቀናቃኞቻቸው አንድም ጊዜ እንዳልተሸነፉ ከታሪካቸው መረዳት ይቻላል። ለኢትየጵያ አንድነት፣ ሉአላዊነት፣ ዘመናዊነት ወዘተ. ይበጃሉ ካሏቸውና ከጀመሯቸው ተግባሮች በተጨማሪ በጀግንነታቸውም የሚታወቁ መሪ ናቸው። እነዚኽ ተግባሮቻቸው ኢትዮጵያውያን የረጅም ልቦልድ እና የተውኔት ፀሓፊዎችን ትኩረት ለመሳብ አስችለዋል (Taye, 1983)።

ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የዝኆን ጠባይ በነገሡባቸው ዕለት የሚፈጽሟቸውን ድርጊቶች ለመረዳት የዝኆንን ጠባይ እና ከዱር አራዊት መካከል ግዙፉ መኾኑን ማስረዳት ያስፈልጋል። ዝኆን በአካላዊ ግዝፈቱ፣ በጉልበቱ፣ በኃይሉ እና በአሸናፊነቱ በየብስ ላይ ካሉት አራዊት ኹሉ ይበልጣል (ደስታ፣ ፲፱፻፷፪፤ ፬፻፹፭)። ዝኆን በየብስ ላይ ያሉትን አራዊት ኹሉ ይበልጣል። ረዥም ኵንቢ እና ወደ ውጪ ገጥጠው ረዝመው የወጡ ጥርሶች አሉት። ኵንቢውም ውሃ ስቦ ለመጠጣት፣ ከዛፍ ቅርንጫፍ ቅጠል ቀጥፎ ወደ አፉ ለማስገባት፣ ጠላቱን ይዞ ለማጥቃት፣ የኀይሉ፣ የብርታቱ፣ የጉልበቱ መሣሪያ እጁ ኾኖ ያገለግለዋል (ደስታ፣ ፲፱፻፷፪፤ ፮፻፵፰)። በምሳሌያዊ ንግግርም ዝኆን ቂጡን ተማምኖ ግንድ ይውጣል” መባሉ በአካሉ በግዙፍነት ሌላው እንስሳ የማያደርገውን ያደርጋል መባሉን ያስገነዝባል። ዝኆን ግዙፍነቱን እና ጉልበቱን ተማምኖ ጫካውን፣ ውድማውን እየጣሰ መኼዱ፣ መንገድ አለመምረጡ፣ ሥርዓት አለመከተሉ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ተቀናቃኞቻቸውን ለማጥቃት ጫካውን እና ውድማውን በኃይል፣ በጉልበት እየጣሱ፣ እየደረማመሱ የተጓዙበትን ወጣ ገባ መንገድ፣ የጣሱትን ጫካ፣ የወጡትን አቀበት፣ የወረዱትን ቁልቁለት እና የወሰዱትን የኃይል ርምጃ ይገልጻል። በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ላይ የዝኆን ጠባይ መንገሡ፣ መሰልጠኑ፣ ዝኆን ከዱር አውሬ እንደሚበልጠው ኹሉ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስም በንጉሥነታቸው ያገር፣ የሕዝብ አውራነታቸውን ይገልጻል። ከማንኛውም ሰው መብለጣቸውን፣ ግርማቸው ትልቅ እና አስፈሪ፣ ሥልጣናቸውም ትልቅ መኾኑን ይጠቁማል። “ከሰው መርጦ ለሹመት፣ ከዕንጨት መርጦ ለታቦት” እንደሚባለው ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የነገሡት እግዚአብሔር ሕዝብን

እንዲያስተዳድሩ፣ እንዲመሩ ትልቅ አድርጎ ስለ መረጣቸው ነው።[6] አንድም፣ ዝኖን ትልቅነቱን፣ ግዙፍነቱን ተማምኖ ጫካውን፣ ውድማውን እንደሚጥሰው ኹሉ፣ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስም ጉልበታቸውን ተማምነው፣ ኃይላቸውን ተመክተው ሰዎችን ቀጥተዋል፤ ለጠሉት እሳት፣ ስለት ሰጥተዋል ማለት ነው። አንድም፣ ሕግ እና ሥርዓት አለማክበራቸውን፣ ፍትሕን ማጉደላቸውን በተለይም በኋለኛው የሥልጣን ዘመናቸው የፈጸሟቸውን የጭካኔ ርምጃዎቻቸውን ይገልጻል።

በቃል ግጥሞቹ እንደተገለጸው በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ላይ የሚነግሠው ጠባይ ከተጠቀሱት እንስሳት ብቻ ሳይኾን ከሰይጣንም፣ ከመልአክም ነው። የሰይጣን ጠባይ ይነግሥባቸዋል የተባለውን ለመግለጽ በቅድሚያ የሰይጣንን አፈጣጠር፣ ማንነት እና ጠባይ በአጭሩ መግለጽ አስፈላጊ ነው። ሰይጣን በመጀመሪያ ቅዱስ ኾኖ ተፈጠረ፤ በኋላ ግን በትዕቢቱ ወደቀ (ኢሳ. 14፣ 12-20፤ ሕዝ. 28፣ 12-19 1ጢሞ. 3፣ 6)። ከወደቀ በኋላ "ይኽን ዓለም በጨለማ የሚገዛ፣ በክፋት የገነነ፣ የግዜርና የሰው መዠመሪያ እና መጨረሻ ጠላት፣ በላይ በታች የሚገኝ" [በሰማይም፣ በምድርም የሚገኝ] ፍጡር ኾነ (ደስታ፣ ፲፱፻፷፪፤ ፪፻፹፱)። ሰይጣን ቅዱስ ኾኖ እንደ ተፈጠረው ኹሉ፣ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ለሥልጣነ መንግሥት እንደበቁ ፍትሕን የሚያሰፍኑ፣ ድኻ ተበደለ፣ ፍርድ ጎደለ የሚሉ ነበሩ። ሰይጣን ከወደቀ በኋላ በክፋት የገነነ እንደኾነው ኹሉ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስም ለሀገራቸው ለማምጣት የፈለጉት ለውጥ እንቅፋት ሲገጥመው ለዚኽ ተጠያቂ ካደረጓቸው ሰዎች ጋር ግጭት ውስጥ ገቡ። ምኞታቸውን ያሰናክላሉ ባሏቸው ላይ የኃይል ርምጃ የወሰዱበት መንገድ ክፉ አስባላቸው። እግዚአብሔርን የሚፃረረውን እና መልካም የኾነውን ነገር ኹሉ የሚቃወመው የሰይጣን ጠባይ በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ላይ በሚነግሥበት ዕለት በሚመሩት ሕዝብ ላይ የሚፈጽሙት እኩይ ድርጊት ከሰይጣን ተግባር ጋራ ይመሳሰላል። ተግባራቸውም የመልካም አስተዳደር ተቃራኒ ነው። ሰይጣን "ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ እንደ ነበረ፣ እውነትም በእሱ እንዳልነበረ" (ዮሐ. 8፣ 44) ኹሉ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስም የሰይጣንን ጠባይ በሚነግሥባቸው ዕለት ጉልበታቸውን ተማምነው እና ሥልጣናቸውን ተመክተው ይመሩት በነበረው ሕዝብ ላይ በፍትሐ ነገሥት ከተደነገገው ውጪ ሰዎችን በሞት መቅጣታቸው ክፉ ድርጊት እንደ ፈጸሙ ያስቆጥራቸዋል። ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ተቀናቃኞቻቸውን በሞት ለመቅጣታቸው የሚከተሉት በማስረጃነት ይጠቀሳሉ። አንደኛ፣ እንጅባራ በተባለው ቦታ ተድላ ጓሉን ድል አድርገው የማረኳቸውን ፯ ሺሕ ወታደሮች "እንደ ይሎ ([ቋሚ እንጨት] ተራ አቁመው በማገር አስማግረው በጠመንጃና በጎራዴ ፈጇቸው" (ሥርግው ገላው፣ 2008፤232)። ኹለተኛ፣ በጋረድ ጭፍራዎች ላይ የሞት ቅጣት ፈጸሙ። ጋረድ ከዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ጋራ ሲዋጋ በጦርነት ሲገደል፤ በርካታ ነፍጠኞቹ ደግሞ ተማረኩ። ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስም የተማረኩትን የጋረድን ኹሉንም ነፍጠኞች ዐንገታቸውን በመቅላት እንዲገደሉ አደረጉ (ዊዳሌ፣ ፲፰፻፺፯)። ሦስተኛ፣ አንኮበር ላይ ከአቤቶ ሰይፉ ሚካኤል ጋር ባደረጉት ጦርነት የማረኳቸውን ወታደሮች ገድለዋል (ኅብረ ሥላሴ፣ ፲፱፻፶፱።

[6] "ከአጼ ኢዮአስ ወዲህ ሐበሻ ተዋርዶ የነበረውን በጉልበትና በስም አኮራት [አኮራው]። ከፍ ከፍ አደረጋት[አደረገው]። ክርስቶስም ውርደትዋን [ውርደቱን]በቃ ሲል ኃይሉን ለአጼ ቴዎድሮስ ሰጠ። በቀኝ በግራ የነበረውን ሁሉ መሳፍንት እየቀጠቀጠ አስታጠቀው" (ሥርግው ገላው፣ 2008፣ 214)።

ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የመልአክነት ጠባይ እንደሚነግሥባቸው በተራ ቁጥር ፩ እና ፫ በተጠቀሱት የቃል ግጥሞች ተገልጿል። መልአክም የግዜር መልእክተኛ ሰማያዊ ረቂቅ ፍጥረት ነው። ከመልአክ ተግባሮች መካከል እግዚአብሔርን የሚፈሩትን ይጠብቃል (መዝ. 34፣ 7)፤ ስለ ታናናሾች በእግዚአብሔር ፊት ይቆማል (ማቴ. 18፣ 10) የሚሉትን እና ሌሎችንም ይፈጽማል። የተጠቀሱትን መልካም ተግባሮች የሚፈጽመው መልአክ ጠባዩ በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ላይ ሲነግሥ ለራበው የሚጎርሰው፣ ለታረዘው የሚለብሰው በመስጠት እና እንዲሰጠው በማዘዝ የርኅራኄ፣ የደግነት፣ የለጋሥነት እና የቸርነት ድርጊት ይፈጽማሉ። ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ በመጀመሪያዎቹ የንግሥናቸው ዓመታት የተጠቀሱትን መልካም ተግባሮች ይፈጽሙ እንደ ነበር ታሪካቸው ያስረዳል። ደግነት፣ ሩኅሩኅነት እና ይቅርባይነት ለሕዝባቸው ከነበራቸው ታማኝነት፣ አገልጋይነት እና አባታዊ ኃላፊነት የፈለቁ ጠባዮቻቸው ነበሩ (መርዕድ፣ 1990)። ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ለድኾች እና ለአቅመ ደካሞች አዛኝ እና ተጨናቂ ነበሩ። በጎ ምግባራቸውንም መርዕድ (1990፤ 101) ቫልድሜዬርን ጠቅሰው "ቴዎድሮስ በመንገድ ሲያልፉ አንድ ችግረኛ ባልቴት ወድቃ ቢያዩ ከፈረሳቸው ወርደው የለበሱትን ሸማ አንስተው [ከላያቸው አውልቀው] ደረቡላት። ቫልድሜዬር ያለውን ብር እንዲያበድራቸው ጠየቁት እና የነበረውን አምስት ብር ተቀብለው ሰጧት። ለቫልድሜዬርም አምስት ብሩን አንድ መቶ አድርገው መለሱለት።" በማለት ከዘገቡት መረዳት ይቻላል። በጦር ሜዳ የማረኳቸውንም "ስለ መድኃኔ ዓለም ብለው ይምሯቸው" ነበር። ለምሳሌ፣ ዋግሹም ገብረ መድኅን የራስ አሊ ተከታይ ሆነው በአይሻል ሜዳ ቈስለው ተማረኩ። ካሳ አስታመው ካዳኗቸው በኋላ፤ "አይዞዎ" ብለው መቶ ነፍጥ ሰጥተው አገራቸውን አገውን ሹመው ሰደዷቸው (መርዕድ፣ 1990፤ 101)።

የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ጠባዮች ሥሪት ከአራት ሰማያዊ እና ምድራዊ ፍጥረቶች ነው መባሉ "በምድር ያለ ፍጥረት ኹሉ ሥር ማይ [ውኃ]፣ መሬት፣ ነፋስ፣ እሳት ናቸው" (ኪዳነ ወልድ፣ ፲፱፻፵፰፤ ፪፻፷፪) ከሚለው የክርስትና እምነት አስተምህሮ ጋራ በቁጥር ይመሳሰላል። የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ጠባዮች የተመሠረቱት "ከአራት ባሕርያት ነው" መባሉም በጠባያቸው በመሬት ላይ ካሉ ሕይወት ካላቸው ፍጥረቶች ጋራ ያመሳስላቸዋል። የተጠቀሱት ጠባያት በየተራ በላያቸው ላይ ሲነግሡ በሚመሩት ሕዝብ ላይ ደግ ወይም ክፉ ይፈጽማሉ። ይኹን እንጂ፣ "የኹሉም እንስሳት ጠባይ ከአራት ባሕርያት የተመሠረተ ነው" ከሚለው የክርስትና እምነት አስተምሮ በተለየ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ዐምስተኛ ጠባይ ይነግሥባቸዋል። ዐምስተኛውን ጠባያቸውን ወረሱት የተባሉት ከግስላ ሲኾን ለሞት ያበቃቸውም ይኸው ዐምስተኛው ጠባያቸው ላያቸው ላይ መንገሡ ነው። ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ከግስላ የወረሱትን ጠባይ ለመረዳት ሥርግው ሐብለ ሥላሴም (2000፤ 461) ሰፋ አድርገው የገለጹትን በአዳኝ እና በግስላ መካከል የሚደረገው ትግል እና ውጤት እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሥርግው እንደሚገልጹት አዳኙ በቁመቱ ልክ ክብ ጉድጓድ ቆፍሮ ግስላን ጠርቶ ይሰድባት እና ጉድጓዱ ውስጥ ይገባል። መሰደቧን የሰማችው ግሥላ ትቈጣለች፤ ከተሰደበችበት ቦታም ፈጥና ትደርሳለች። የሰደባትን አዳኝ ለማጥቃት የከለለበትን ጋሻ በመንጠቅ ራሱን ከደበቀበት ጉድጓድ ለማውጣት ትግል ታደርጋለች። አዳኙም ጉድጓዱ ውስጥ ኾኖ የጉድጓዱን አፍ በጋሻው ዘግቶ ይዞ ስድቡን ይቀጥላል። ግስላዋም የጉድጓዱን ክዳን በመክፈት የሰደባትን አዳኝ ለመበቀል በሙሉ ኀይሏ

ጥቃት ትሰነዝራለች። አዳኙ ደግሞ በቈፈረው ጉድጓድ ውስጥ ኾኖ ጋሻውን አጥብቆ በመያዝ ለረጅም ሰዓታት ይታገላል። በአዳኙ ብርቱ ትግል ግስላዋ ጥቃቱን ማድረስ ይሳናታል። በዚኽ ጊዜ ትናደድና ራሷን አንቃ ትገላለች (ሥርግው ሐብለ ሥላሴ፣ 2000፤ 463)። ይኽንን የግስላ ጠባይ ደስታም (፲፱፻፷፪፤ ፫፻፲፰) "ግስላ ዐዳኝ በጉድጓድ ውስጥ ተቀምጦ ጋሻ ለብሶ ሲሰድባት ጋሻውን መንጠቅ እና ዐዳኙን መግደል ባቃታት (በተሳናት) ጊዜ በገዛ እጇ ታንቃ ትሞታለች ይላሉ" በማለት በስም ካልተገለጹ ሰዎች የሰሙትን ይገልጻሉ። ግስላ በጠባይዋ ያሰበችውን ጥቃት በሰው ላይ መፈጸም ባለመቻሏ ተበሳጭታ ራሷን እንደምትገድለው ኹሉ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስም የግስላ ጠባይ ሲነግሥባቸው ዓላማቸውን በኃይል ለማሳካት የተከተሉት መንገድ ራሳቸውን ለመግደል አድርሷቸዋል። የግስላ ጠባይ የነገሠባቸው ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ በእልኸኛነታቸው ያስከፋቸውን ኹሉ በኃይል እና በጉልበት መምራታቸው ለሞት እንዳበቃቸው የቃል ግጥሞቹ ይገልጻሉ።

ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የአንበሳ፣ የዝኆን፣ የሰይጣን እና የመልአክ ጠባዮች እየተፈራረቁ እንደሚሾሙባቸው በተራ ቁጥር ፩ እና ፫ በተጠቀሱት የቃል ግጥሞች በተመሳሳይ ይገልጻሉ። ነገር ግን በተራ ቁጥር ፫ የተጠቀሰው የቃል ግጥም የመጨረሻው ሥንኝ በተራ ቁጥር ፩፣ ፪ እና ፬ ከተጠቀሱት የቃል ግጥሞች ይለያል። በሌሎቹ ተራ ቁጥሮች በተጠቀሱት የቃል ግጥሞች የሚነበበው የመጨረሻው ሥንኝ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ራሳቸውን የገደሉት ላያቸው ላይ የግሥላ ጠባይ በመንገሡ መኾኑ ሲገለጽ በተራ ቁጥር ፫ በተጠቀሰው ደግሞ ራሳቸውን የመግደላቸው ታሪካዊ እውነታ እንጂ ለሞት የዳረጋቸው የጠባይ ለውጥ ምን እንደ ነበር አይገልጽም። በሌሎቹ ተራ ቁጥሮች በተጠቀሱት የቃል ግጥሞች ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን ለሞት የዳረጋቸው የግስላን የእልኸኛነት፣ የኃይለኛነት፣ የጀብደኝነት እና "የአሸንፋለሁ" ባይነት አጉል ወይም ትክክል ያልኾነ ጠባይ በመውረሳቸው መኾኑን በመግለጽ ጥፋተኛ ያደርጋቸዋል። በተራ ቀጥር ፫ በተጠቀሰው የቃል ግጥም ራሳቸውን የገደሉት የሌላን ጠባይ ሳይወርሱ በሰውነታቸው ለራሳቸውም፣ ለሀገራቸውም ክብር ሲሉ የፈጸሙት ተግባር ተደርጎ የሚገለጽ በመኾኑ ያስመሰግናቸዋል፤ ያስሞግሳቸዋል። በሽጉጣቸው ራሳቸውን የገደሉትም ከእንግሊዝ ጦር ጥቃት እንዳላመለጡ ባወቁ ጊዜ "በጠላት እጅ ከምሞት" ብለው ነው (ሥርግው ገላው፣ 2008፤ 241-242)። ይኽ ድርጊታቸው የራስንም፣ የሀገርንም ክብር ለመጠበቅ በራስ ላይ የወሰኑት ውሳኔ መኾኑን ያስረዳል። ይኽንን ድርጊታቸውን መነሻ አድርገውም የተለያዩ የፈጠራ ሰዎች በልዩ ልዩ ሥራዎቻቸው እያሞገሷቸው ይገኛሉ።

በተራ ቁጥር ፫ የተጠቀሰው የቃል ግጥም የመጨረሻው ሥንኝ የሐረግ ምጣኔ እና ይዘት በሌሎቹ ቁጥሮች ከተጠቀሱት ይለያል። ይኽ ልዩነትም በቃል ግጥሙ የቅርጽም፣ የይዘትም ልውጠት እንዲፈጠር አድርጓል። የቅርጽም፣ የይዘትም ልውጠት ቢኖርበትም የቃል ግጥም ግን በበገና ደርዳሪው አንደበት እየተዜመ ለአድማጭ ይተላለፋል።

በተራ ቁጥር ፬ በተጠቀሰው የቃል ግጥም ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የተለያዩ ጠባዮች እንደ አሏቸው "ቆንጥረው ቆንጥረው ሁሉን ያካበቱ" በሚለው ሥንኝ ይገለጽ እንጂ ምንነታቸው ግን አልተገለጸም። በሌሎች ተራ ቁጥሮች በተጠቀሱት የቃል ግጥሞች ጠባዮቻቸውን ከአንበሳ፣ ከዝኆን፣ ከመልአክ

እና ከሰይጣን እንደሚወርሱ የተገለጹት በተራ ቁጥር ፬ በተጠቀሰው የቃል ግጥም አልተገለጹም። በሌሎቹ የቃል ግጥሞች እንደሚነግሡባቸው የተገለጹት ጠባዮች የአንበሳ ጀግንነታቸውን እና አሸናፊነታቸውን፣ የዝኆን ትልቅነታቸውን እና ንጉሥነታቸውን፣ የመልአክ ደግነታቸውን እና ሩኅሩኅነታቸውን የሰይጣን ደግሞ ክፉነታቸውን እና ጭካኝነታቸውን ይገልጻሉ። በተራ ቁጥር ፩፣ ፪ እና ፬ የተጠቀሱት የቃል ግጥሞች በተመሳሳይ የግስላ ጠባይ ሲነግሥባቸው ለሞት መዳረጋቸውን ይገልጻሉ። በተራ ቁጥር ፪ እና ፬ በተጠቀሱት የቃል ግጥሞች የተለያዩ ጠባዮቻቸውን የሚገልጹት ሥንኞች ተሟልተው አለመመዝገባቸው የቅርጽም፣ የይዘትም ልውጠት እንዲፈጠር አድርጓል። የቅርጽ ልውጠቱ ሥንኞች በኹሉም የቃል ግጥሞች አለመመዝገባቸው ነው። የይዘት ልውጠቱ ደግሞ የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን የተለያዩ ጠባዮች የሚገልጹት በሥንኞች በኹሉም የቃል ግጥሞች እኩል ተሟልተው አለመመመዝገባቸው ያስከተለው ነው።

በተራ ቁጥር ፩፣ ፪ እና ፬ የተጠቀሱት የቃል ግጥሞች "የመጨረሻው ዕለት መቅደላ አፋፉ ላይ ግስላ ኾኑና ታነቁና ሞቱ" በማለት የተጠቀሰው ሥንኝ ለሞት የተዳረጉት "በራሳቸው ጥፋት ነው" ብሎ ማመንን ይገልጻል። በሥንኙ የተገለጸው "ራሳቸውን ለመግደል ያደርሳቸውን ድርጊት የፈጸሙት በልኸኛነታቸው፣ በጀብደኛነታቸው፣ ኹሉንም ላሸንፍ ባይነታቸው ነው" የሚለው ይዘት በጽሑፍ ተመዝግቦ ከሚገኘው ታሪካቸው ጋር በማነጻጸር መረዳት አስፈላጊ ነው። ይኽንንም ስለዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የመጨረሻዎቹ የሥልጣን ዘመናት ባሕሩ (፪ሺህ፡ 42) የገለጹትን የሚከተለውን በመጥቀስ ማስረዳት አስፈላጊ ነው።

> የመጨረሻ ዓመታት በውስጥም ሆነ በውጭ ፅልመትን የተላበሱ ነበሩ። በውስጥ ግዛት ከግዛት ሳይለይ አጠቃላይ አመፅ ተነሣበት። በውጭም ቢሆን እርዱኝ ብሎ እጁን ከዘረጋላቸው አውሮጳውያን ያገኘው መልስ ዝምታ ወይም ንቀት ብቻ ነበር። በጭንቀትና ከመከፋት የተነሣ ጭካኔን መፍትሔ አድርጎ ያዘው። ጠላቱንና ወዳጁን መለየት አልቻለም። ሁሉም ላይ የቁጣው መቅሠፍት እኩል ወረደባቸው። ይህም ሁኔታውን አባባሰው። በውስጥም ጠላቶቹን ይበልጥ አበራከተበት፤ በውጭ ደግሞ ለፍቅርና ለወዳጅነት ደብዳቤዎቹ ደንታ ያልሰጡትን እንግሊዞች አስነሣበት። ሊረዱት ያልተዘጋጁት ሊያጠፉት ተነሡ።

"ለፍትሕና ለእኩልነት መቆርቆር" (ባሕሩ ፣ ፪ሺህ፤ 38) የነበራቸውን ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ መንገዳቸውን ባጨለሙባቸው የሀገር ውስጥ ተቃዋሚዎቻቸው ላይ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ይፈጽሙት የነበረው የኃይል አማራጭ ጠላት አብዝቶባቸዋል። ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጋራ የፈጠሩት ግጭት በቤተ ክርስቲያኗ መሪዎች እና በካህናቱ ዘንድ ተቀባይነታቸውን ቀንሶባቸዋል፤ ጠላቶቻቸውንም አበርትቶባቸዋል። በጠባያቸው መለዋወጥ እና በሚወስዷቸው የቅጣት ርምጃዎች በግዛታቸው የሚኖረው ሕዝብ ተስፋ እንዲቆርጥ አድርጎታል። በመጀመሪያዎቹ የሥልጣን ዘመናቸው የለውጥ ርምጃዎቻቸውን ይደግፍ የነበረው የኅብረተሰብ ክፍል እሳቸውን መጥላቱን የተገነዘቡ አንዳንድ መሳፍንት አጋጣሚውን ተጠቅመው

ዐምፀውባቸዋል። እሳቸውን መሪ አድርጎ ይከተላቸው የነበረው ሰራዊታቸው እየጣላቸው መኼድ ቀጥሏል። ወደ መቅደላ ሲኼዱ የነበራቸው ተዋጊ ኃይል ብዛት በመጀመሪያዎቹ የሥልጣን ዘመናቸው ከነበረው በእጅጉ ቀንሶ ነበር። የእንግሊዝን ጦር ለመከላከል ወደ መቅደላ ሲጓዙ በመንገዳቸው ያለውን ሕዝባቸውን እና አባታቸውን የገደሉባቸውን ዋግሹም ጎበዜን በሥጋት መመልከታቸው በተቃዋሚዎቻቸው ላይ የወሰዱት ቅጣት ያስከተለባቸው ነው (ተክለ ጻድቅ፣ ፲፱፻፹፪)። ከእንግሊዝ ወረራ በፊት የጎጃም፣ የትግራይ እና የሸዋ ገዢዎች ዐምፀው ከዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ እጅ ወጥተው ነበር ማለት ይቻላል። የእሳቸው እንቅስቃሴም በመቅደላ እና አካባቢው ላይ የተገደበ ነበር (ባሕሩ፣ ፪ሺ፱)።

ሊያጠቃቸው የዘመተባቸው የእንግሊዝ ጦር ወደ ኢትዮጵያ የመምጣቱ ምክንያት ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ በእንግሊዛውያን ላይ የወሰዱት የእስር ርምጃ ነበር። በእንግሊዞቹ ስሌት መሠረት "አውሮጳውያንን ለማሰር የሚጋበዝ የአፍሪቃ መሪ በቸልታ ሊታለፍ አይገባውም ነበር" (ባሕሩ፣ ፪ሺ፱፤ 42)። የእንግሊዝን ተወላጆች ባያስሩ ኖሮ የእንግሊዝ ጦር አይዘምትባቸውም፤ ጥቃትም አይከፈተባቸውም ነበር ተብሎ ይታመናል።ለእንግሊዝ ጦር ጥቃት የዳረጋቸው የውጭ ግንኙነት ልምድ አለመኖር እንደኾነም ይገለጻል (Venkataram, 1973)።

በቃል ግጥሞች የተነገረው ይዘት መቅደላ ላይ ራሳቸውን በራሳቸው ለመግደል ያደረሳቸውን ስሕተት የፈጸሙት ራሳቸው ናቸው። በቃል ግጥሞቹ የተነገረውም ሮቢንሰን (Rubenson) (1966) የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ውድቀት ዋናው ምክንያት ውስጣዊ ችግሮቻቸውን መፍታት አለመቻላቸው ነው በማለት ከገለጹት እና ክራሚ (Crummey) (1969፡ 1971) ቴዎድሮስ ራሳቸውን አጠፉ እንጂ የእንግሊዝ ጦር አላጠፋቸውም ካሉት ጋራ ይጣጣማል። ይኹን እንጂ፣ በቃል ግጥሞቹ በተላለፈው ይዘት ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ራሳቸውን የገደሉት በራሳቸው ጥፋት አድርጎ መግለጹ በሀገር ውስጥ የገጠማቸውን የለውጥ እንቅፋት እና የውጭ ግንኙነት ጥያቄአቸው በዝምታ ወይም በንቀት መታለፍ ያደረሰባቸውን የስሜት ስብራት ያገናዘበ አይደለም።

ከዚኽ በላይ የተመረመሩት የቃል ግጥሞች የቅርጽም፣ የይዘትም ልውጠት ይታይባቸዋል። የቅርጽም፣ ይዘትም ልውጠቶቹ ሥንኝ በመቀነስ እና በሐረግ ውስጥ ያሉትን ቃላት በመለወጥ የተፈጠሩ ናቸው። እንደዚኹም በተራ ቁጥር ፬ በተጠቀሰው የቃል ግጥም በሌሎቹ ተራ ቁጥሮች የተጠቀሱት ሥንኞች ተሟልተው አለመጠቀስ የቅርጽም፣ የይዘትም ልውጠት እዲፈጠር አድርጓል። ተለውጠው የተመዘገቡት የቃል ግጥሞች በየራሳቸው ዐውዳዊ ቁመና በየተመዘገቡበት ሥራ ውስጥ ለአንባቢ ይተላለፋሉ። በየሥራዎቹ ተለውጠው የተመዘገቡት የቃል ግጥሞች ሲተላለፉ አንባቢው እንደ ትክክል ቆጥሮ ይቀበላቸዋል እንጂ ልውጠት መኖሩን ላይገነዘብ ይችላል። በአንዳንድ የቃል ግጥሞች የቅርጽም፣ የይዘትም ልውጠት መኖሩን በቀላሉ ለመገንዘብ እንደሚያስቸግር ቀጥሎ በሚቀርበው ንዑስ ርእስ እንመለከታለን።

4) የቃል ግጥም ይዘት ልውጠት እና ታሪካዊ እውነት

ስለ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የተዜሙት የቃል ግጥሞች የቅርጽም፣ የይዘትም ልውጠት እንደሚታይባቸው ቀደም ሲል ተገልጿል። የይዘት ልውጠቱም በታሪክ ሰነዶች ከተመዘገበው የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ታሪክ ጋራ ሲነጻጸር ግልጽ እና ቁርጥ ያለ መልስ ለማግኘት የሚቸግርበት ኹኔታ ያጋጥማል። ለዚኽ ማስረጃ ከዚኽ በታች የተጠቀሱትን የቃል ግጥሞች እንመረምራለን።

፩) ጋረድ ሞተ እንኳ ተቀበረ፤
ያንተ ዘር ነውና ሠግተነው ነበረ
(ፉሴላ፣ 1958: 91፤ ተክለ ጻድቅ ፣ ፲፱የ፹፩፤ 219)።

፪) ጋረድ ሞተ እንኳ ተቀበረ፤
ያንተ ወንድም ነውና እንፈራው ነበረ
(ዌዳሌ፣ 1897፤ 23፤ ገሪማ፣ ፲፱የ፺፪፤ የ፵፬፤ ሥርግው ገላው፣ 2008፤ 223)።

በተራ ቀጥር ፩ የተጠቀሰው የቃል ግጥም የቀረበበት ዐውድ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ጋረድን ድል አድርገው እና ገድለው ከእሱ ጎን ተሰልፎ ሲዋጋ የነበረውን እና የተማረከውን ሠራዊት በሞት ቀጥተው ጎንደር በድል ገብተው ባዳራሽ ግብር ባገቡበት ዕለት አዝማሪው በግብር ላይ ተነሥቶ የገጠመው መኾኑን ተክለ ጻድቅ (፲፱የ፹፩፤ 219) ይገልጻሉ።

የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ አዝማሪ ግብር በቀረበበት አዳራሽ ተገኝቶ ያዜመው ይኽ የቃል ግጥም በፉሴላ የተመዘገበው እና በተራ ቁጥር ፩ የተጠቀሰው መኾኑን ተክለ ጻድቅ አክለው ገልጸዋል። በተራ ቁጥር ፪ የተጠቀሰውን የቃል ግጥም የመዘገቡት ጸሓፍት ግን በማን እንደ ተዜመ አልገለጹም (ገሪማ፣ ፲፱የ፺፪፤ ሥርግው ገላው፣ 2008)።

በቃል ግጥሞቹ የሚነበቡበት "ዘር" እና "ወንድም" የሚሉት ቃላት በቁማቸው ሲመለከቷቸው ተቀራራቢ ፍቺ እና አገልግሎት ያላቸው፣ አንዱ ሌላውን የሚተካ ይመስላል። ቃላቱ በዐውዳዊ አገልግሎታቸው የዝምድና ቅርበትን የሚገልጹ ቢመስልም በጥልቀት ሲመረመሩ ግን ያን አይገልጹም። የቃላቱ ዐውዳ ፍቻቸው እንደሚከተለው ቀርቧል።

በተራ ቁጥር ፩ የተጠቀሰው የቃል ግጥም ኹለተኛው ሥንኝ "ዘር" የሚለው ቃል ፍቺ፣ በትውልድ የአባት ወይም የእናት ወገን የኾነ ሰው (ለምሳሌ፣ ታናሽ ወይም ታላቅ ወንድም፣ የወንድም ልጅ፣ አጎት፣ የአጎት ወይም የአክስት ልጅ እያሉ እስከ ሰባት ትውልድ የሚቈጠር የሥጋ ዝምድና) ማለት ነው። አንድም፣ የአንድ ጎሣ ወይም ማኅበረሰብ አባል መኾን ማለት ነው። እንደዚኹም፣ በተራ ቁጥር ፪ በተጠቀሰው የቃል ግጥም ኹለተኛው ሥንኝ ላይ የሚነበበው "ወንድም" የሚለው ቃል ፍቺ፣ አንድም፣ ከእናት ወይም ከአባት ወይም ከኹለቱም በመወለድ የሚገኝ ሰው ዝምድና መጠሪያ ነው። አንድም፣ የወንድም ወይም የአክስት ወይም የአጎት ወይም የቅርብ ዘመድ ወንድ ልጅ ነው። በዐማርኛ ቋንቋ ተናጋሪው ኅብረተሰብ "ወንድም" የሚለው መጠሪያ የአጎትንም ልጅ፣ የወንድምንም ልጅ ዝምድና ለመግለጽ ያገለግላል (ብርሃኑ አበበ፣ ፲፱የ፸፫፤ 36)። አንድም፣ እንደ እናት ልጅ የሚቈጠር፣ ወዳጅ፣ ባልንጀራ፣ ጓደኛ ማለት ነው። አንድም፣ የዕድሜ እኩያ ወይም ታላቅ ወይም

ታናሽ መጥረያ ነው። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (1993) በተዘጋጀው <u>አማርኛ መዝገበ ቃላት</u> "ዘር" እና "ወንድም" ለሚሉት ቃላት የተሰጡት ፍቺዎች በቅርበት ሲመረመሩ ከ "ዘር" ይልቅ "ወንድም" የሚለው የዝምድና ቅርበትን ይገልጻል። "ዘር" የዝምድና ርቀትን፣ "ወንድም" ደግሞ የዝምድና ቅርበትን እንደሚገልጹ ለየቃላቱ ከተሰጠው የመዝገበ ቃላት ፍቺ መረዳት ይቻላል። የዝምድና መጠሪያው በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ታሪክ ከተመዘገበው ጋራ ሲነጻጸር ግልጽ ባለመንገድ መልስ ማግኘት ያስቸግራል። የዚኽም ምክንያት በታሪክ የተመዘገበው የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ እና የጋረድ ዝምድና የተለያየ ተደርጎ መመዝገቡ ነው። በቃል ግጥሞቹ የሚነበቡት ኹለቱ የተለያዩ ቃላት በየራሳቸው የገለጹትን የዝምድና ቅርበት ለመወሰን በታሪክ መጻሕፍት የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ እና የጋረድ ዝምድና እንዴት እንደተገለጸ መረዳት አስፈላጊ ነው።

በተጠቀሱት የቃል ግጥሞች እንደተገለጸው የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ እና የጋረድ ዝምድና በታሪክ ድርሳናትም በወጥነት በአንድ ዓይነት አይጠራም። ፉሴላ (1958) ጋረድን አንድ ጊዜ የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የአኅት ልጅ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ የወንድም ልጅ አድርገው ለዋውጠው ይገልጻሉ። ፉሴላ (1958: 69) እንደሚገልጹት "የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ያባታቸው ስም ወልደ ጊዮርጊስ ኃይሉ ይባላል። የደጃች ክንፉ ወንድም ናቸው።" ደጃዝማች ክንፉ የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ አባት የደጃዝማች ኃይሉ ወንድም ከኾኑ የጋረድ አባት ደጃዝማች ክንፉ ደግሞ የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ አጎት፣ ልጃቸው ጋረድ ደግሞ የአጎታቸው ልጅ ናቸው ማለት ነው። ፉሴላ (1958፤ 69) አክለውም ደጃዝማች ክንፉ የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የአባታቸው ወንድም የእሳቸው ደግሞ አጎታቸው ስለ መኾናቸው "ደጃዝማች ካሣ በልጅነታቸው ወደ አጎታቸው ወደ ደጃዝማች ክንፉ ቤት ኼደው አደጉ" በማለት ይገልጻሉ። "ጋረድ የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የአጎታቸው ልጅ ናቸው" የሚለውን የፉሴላ የዝምድና ቆጠራ ደግፎ ዊዳሴም (1897፤ 22) ልጅ ጋረድ የሚባል ያጎትዎ ልጅ ሽፍታ ተነስቶ ሀገር ይዘርፍ ዠመር" በማለት ይገልጻል። ይኽም በፉሴላ "ደጃዝማች ክንፉ የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ አጎት ናቸው" የሚለው የዝምድና አቈጣጠር በሌሎች ሰዎች ዘንድ ተቀባይነት እንደ ነበረው ያስገነዝባል።

ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ በደጃዝማች ክንፉ ቤት (በኃይሉ ወንድም ቤት) ማደጋቸው ባጎታቸው እንዲኮሩ፣ እንዲሞገሱ አድርጓቸዋል የሚል ግንዛቤም ይፈጥራል። የደጃዝማች ኃይሉን የዘር ሐረግ ትልቅ ያስባለው የወንድማቸው የክንፉ መስፍንነት፣ የሰፊ ግዛት ባለቤትነት፣ ዐርበኝነት እና ታዋቂነት መኾኑ ነው። ጋረድን የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የአኅት ልጅ አድርጎ የገለጸው ፉሴላ ሌላ ጊዜ ደጃዝማች ክንፉ የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ወንድም መኾናቸውን "ክንፉ ጋረድ የአጤ ቴዎድሮስ የወንድም ልጅ ነው። አጤ ቴዎድሮስ በአባቱ በደጃች ክንፉ ይምሉ ነበር። ክንፉ ይሙት ይላሉ። ሲፈክሩም የመይሳ ልጅ ይሉ ነበር። ደጃች ክንፉ ስለ አሳደግዋቸው" በማለት ገልጸዋል (ፉሴላ፣ 1958፤ 87)። ይኹን እንጂ፣ "መይሳው" የሚለውን የጀግንነት ተግባር መግለጫ ቃል ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ራሳቸውን ለመግለጽ ይጠቀሙበት እንደ ነበር ደስታ (፲፱፻፷፪፤ ፪፻፷፫)፦

እኔ መዩ ነጭ ባይ፣
የምሸሽ ነኝ ወይ።

በማለት የመዘገቡት ያስረዳል። (የዚኽ የቃል ግጥም የመጀመሪያው ስንኝ "እኔ መዩ ቱርክ ባይ" በማለትም ይነገራል።)

ብርሃኑ (፲፱፻፸፰፣ 35-36) በበኩላቸው በቅርቡ ከካይሮ ብሔራዊ ቤተ መዛግብት በማኀደር ቁጥር 19 ተገኝቶ በስዊድናዊው የኢትዮጵያ ታሪክ መምህር በስቨን ሩቤንሰን በቀረበ መረጃ "ሼህ ካሣ ኃይሉ" (ማለት ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ) በዐረብኛ የጻፉት ደብዳቤ "ክንፉ እና እኔ ወንድማማች ነን ያባት ልጆች "የሚል ሐረግ ስለ ተገኘበት ደጃች ክንፉ የአፄ ቴዎድሮስ ወንድማቸው እንጂ አጎታቸው አይደሉም የሚል ጥያቄ ቀስቅሷል" ብለዋል። ብርሃኑ ማስረጃ ጠቅሰው በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ እና በጋረድ አባት በደጃዝማች ክንፉ መካከል የነበረው የዝምድና አቈጣጠር "አጎት ናቸው" ከሚለው የተለየ የዝምድና ቅርበት መኖሩን ገልጸዋል። መርዕድም (እ. ጎ. አ. 1990፣ 69) "ደጃዝማች ክንፉ የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የአባታቸው ልጅ ወንድማቸው ናቸው" ብለዋል። ደጃዝማች ኃይሉ የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን እናት ከማግባታቸው በፊት የደጃዝማች ማሩን ልጅ ወይዘሮ ወለተ ተክሌን አግብተው ከወለዷቸው ልጆች አንደኛው ደጃዝማች ክንፉ እንደኾኑ ይነገራል። ባሕሩም (፪ሺህ፣ 25) ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የደጃዝማች ክንፉ ወንድም (ባባት ወገን) መኾናቸውን ገልጸዋል።

በቃል ግጥሙ የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ እና የጋረድ ዝምድና "ወንድም" በማለት መገለጹ ለታሪካዊ እውነታው የቀረበ ነው ማለት ይቻላል። በፋሴላ "የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የወንድምም፣ የአጎት ልጅም ናቸው" የተባሉት ጋረድ በዊዳሌ "የአጎት ልጅ"፣ በብርሃኑ እና በመርዕድ ደግሞ "የወንደም ልጅ ናቸው" መባሉ ለኹለቱም የዝምድና መጠሪያዎች ማገልገሉን ያስረዳል። ከእናት እና ከአባት ወይም ከአንዳቸው የሚወለድን ወንድ ልጅ "ወንደም" ተብሎ እንደሚጠራው ኹሉ፣ የወንድምን ልጅ፣ የአጎትን ልጅ፣ የአክስትን ልጅ ዝምድና ማቅረብ ሲፈለግ "ወንድም" ብሎ መጥራት በዐማራው ኅብረተሰብ ዘንድ የተለመደ ነው። የቃል ግጥሙም ይኽንኑ አጠራር ተጠቅሟል። በአንጻሩ "ጋረድ የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ዘር" ነው በማለት በቃል ግጥሙ የተገለጸውን እና የዝምድና ርቀትን የሚያመለክተውን ፍቺ የሚደግፍ ሐሳብ ከተጠቀሱት ሰዎች ሥራዎች ማግኘት አልተቻለም።

ይኽ ምረመራ የተደረገው በኹለቱ ተራ ቁጥሮች ከጠቀሱት የቃል ግጥሞች አንደኛውን "ትክክል ነው"፣ ሌላኛውን "ትክክክል አይደለም" የሚል ውሳኔ ለመስጠት አይደለም። የምርመራው ዓላማ በኹለቱ ተራ ቁጥሮች የተጠቀሱት የቃል ግጥሞች በቃላት አጠቃቀም ልዩነት ምክንያት የተፈጠሩትን የቅርጽም፣ የይዘትም ልውጠቶች ማስረዳት እና በታሪክ ሰነዶች ከተመዘገበው ከዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ታሪክ ጋራ ማነጻጸር ብቻ ነው። ለውጡ የተፈጠረው የቃል ግጥሙን ያዜመው አዝማሪ፣ ቀድሞ የሰማውን የቃል ግጥሙ የቃላት አደራደር በትክክል ማስታወስ ባለመቻሉ ዝምድናን ለመግለጽ ከሚያስችሉት "ዘር" እና "ወንድም" ከሚሉት ቃላት አንደኛውን

ተክቶ ተጠቅሟል። አንድም፣ አዝማሪው በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ፊት የቃል ግጥሙን ሲያዜም ኾን ብሎ በማሻሻል የንጉሡን እና የጋረድን የሥጋ የዝምድና ቅርበት ለመግለጽ ተጠቅሞበታል።

በተጠቀሱት የቃል ግጥሞች የሚነበቡት "ሥጋት" እና "ፍርሃት" የሚሉት ቃላት ትርጉማቸው "አንድ ዓይነት" መኾኑን ተክለ ጻድቅ (፲፱፻፹፩፣ 220) በግርጌ ማስታወሻ ተራ ቁጥር ፩ ገልጸዋል። ተክለ ጻድቅ ይኽን ይበሉ እንጂ ቃላቱ በጥልቀት ሲመረመሩ አንድ ዓይነት ዕሳቤን አይገልጹም። "ሥጋት" መጥፎ ወይም ክፉ ነገር ይደርሳል ብሎ መጠርጠርን፣ መገመትን፣ ማሰብን፣ "ፍርሃት" ደግሞ ከዐቅም በላይ የኾነ ከፍተኛ ጉዳት ይደርሳል ብሎ መረበሽን፣ ድፍረት፣ ወኔ ማጣትን፣ መጨነቅን ይገልጻሉ።

ቃላቱ ከዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ እና ከጋረድ የባላንጣነት ሕይወት (ከታሪካዊ ዐውዱ) አንጻር ሲመረመሩ የተለያዩ ስሜቶችን ይገልጻሉ። የጋረድ የሽፍትነት የመጀመሪያዎቹ ዓመታት የሥጋት፣ የኹለተኛዎቹ ደግሞ በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ አገዛዝ ላይ የፍርሃት ስሜቶች እንዳሳደሩ ታሪካቸው ያስረዳል። ጋረድ በመጀመሪያዎቹ የሽፍትነቱ ዓመታት ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስም፣ ጠንካራ ደጋፊዎቻቸውም አሉበት ከሚባል ቦታ ርቆ እና ተሰውሮ ሌሊት በጨረቃ፣ ቀን በፀሓይ እንቅስቀሴ ያደርግ ነበር። በእንቅስቃሴውም ሕዝብን ለዐመፅ ያነሣሣ እና የደፈጣ ጥቃት ለማድረስ ይሞክር ነበር። ይኹን እንጂ፣ ጋረድ በመጀመሪያዎቹ የሽፍትነት ዓመታት የዳግማዊ ዐፄ ቴወድሮስን ተቀናቃኞች በማስተባበር ጉልበቱን አደርጅቶ በአስተዳደራቸው ላይ "ችግር ይፈጥራል"፤ "የሥልጣን ተገዳዳሪያቸው ይኾናል" ተብሎ አልተፈራም። ኾኖም፣ ጋረድ አባቱ ደጃዝማች ክንፉ የነበራቸውን የምስፍና ቦታ ለመያዝ ባሀሉ የሚፈቅድለት የመስፍን ልጅ በመኾኑ በመጀመሪያዎቹ የሽፍትነት ዓመታት በሚያደርገው እንቅስቃሴ በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ዘንድ በሥጋት ይታይ ነበር። ይኽንንም ፋሴላ (1958፤ 87)፡- "ክንፉ ጋረድ ··· አጤ ቴዎድሮስን ከድቶ ብርቱ ሽፍታ ሆኖ ነበር [።] በደምቢያም፣ በጭልጋም ቆላ ለቆላ እየተሰረቀ መሻዳሪ ይበላ ነበር፣ ንጉሡም ዘመዳቸው ስለ ሆነ ችላ ብለውት ነበር፤ ተው ግባ እያሉም ይመክሩት ነበር" በማለት ከገለጹት መረዳት ይቻላል። "ብርቱ ሽፍታ ሆኖ ነበር" የሚለው ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ "ችላ ብለውት ነበር" ከሚለው አገላለጽ ጋራ ሲነጻጸር ብርታቱ አንጻራዊ ነበር ማለት ይቻላል፤ ብርቱ ጠላት ችላ አይባልምና። ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ በሽፍትነት ላይ የነበረውን ጋረድን "እንዲገባ ይመክሩት ነበር" የሚለው አነጋገር ለእሱ የነበራቸውን ዝቅተኛ ግምት ይገልጻል። ከግምታቸው መረዳት የሚቻለው ጋረድ በመሸፈቱ "ችግር ይፈጥራል" የሚል ሥጋት ቢኖራቸውም "ይገዳደረኛል" ብለው አለመፍራታቸውን ነው። ቢፈሩት ኖሮ ከምክር ይልቅ እሱን የሚያጠቃ ጦር ያዘምቱበት ወይም ራሳቸው ይዘምቱበት ነበር። ለዚኽም ይመስላል ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን "ግባ በሉት" የሚል ምክር "ይነገረው" ያሉት።

ከጋረድ የሽፍትነት ታሪክ መገንዘብ እንደሚቻለው በተራ ቁጥር ፩ በተጠቀሰው የቃል ግጥም "ሥጋት" የሚለው ቃል የጋረድን የሽፍትነትና የመዋጋት ዐቅም አለመጎልበትን ይገልጻል። ይኽም በመጀመሪያዎቹ የሽፍትነት ዓመታት ጋረድ የነበረውን የመዋጋት ጉልበት ወይም ዐቅም አለመጎልበት ያስረዳል። በተራ ቁጥር ፪ በተጠቀሰው የቃል ግጥም "ሥጋት" የሚለውን እንዲተካ የተደረገው

“ፍራት” የሚለው ቃል ጋሪድ ኃይሉ የመዋጋት ዐቅሙ የጎለበተበት እና ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን ለመፋለም ዝግጁ የነበረበትን የመጨረሻዎቹን የሽፍትነቱን ዓመታት ይገልጻል። የቃል ግጥሞቹ ሲነጻጸሩ የጋረድን ተከታታይነት እና ቀጣይነት ያለውን የሽፍትነት እንቅስቃሴ እና በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ወታደሮች ወይም ደጋፊዎች ዘንድ የተፈጠሩትን የተለያዩ ስሜቶች ይገልጻሉ። ከቃል ግጥሞቹ የቃላት አጠቃቀም ለውጥ እና ከጋረድ የሽፍትነት ታሪክ መረዳት እንደሚቻለው ለውጡ የቅርጽም፣ የይዘትም ነው።

ለዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ በተዜሙ የቃል ግጥሞች የሚታየው ልውጠት የቅርጽ እና የይዘት ብቻ አይደለም። የአንዳንዶቹ የቃል ግጥሞች የይዘት ልውጠት በጽሑፍ ተመዝግቦ የሚገኘውን የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን ታሪክ አያንፀባርቅም። ከዚኽም በላይ፣ እሳቸው የፈጸሙትን እና የሚታወቀውን ታሪካቸውን ይቃረናል። ይኽንንም ቀጥሎ በሚቀርበው ንዑስ ርእስ እንመለከታለን።

5) በቃል ግጥሞች የሚታዩ ለውጠቶች እና የታሪክ ተፋልሶ

ለዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ በተዜሙ የቃል ግጥሞች የቃላት አጠቃቀም፣ የድርጊት አተራረክ፣ አገላለጽ እና የስሞች አዘራዘር ለውጦች ይታያሉ። በቃል ግጥሞቹ የሚታዩት የአገላለጽ ለውጦች የቅርጽ እንጂ የይዘት ልውጠት አያስከትሉም። እንደዚኹም በቃል ግጥሞቹ የሚዘረዘሩትን (የሚቆጠሩትን) ነገሮች ጨምሮ ወይም ቀንሶ መቁጠር ወይም በሌላ መንገድ መግለጽ በቃል ግጥሞች ማስተላለፍ የተፈለገውን ይዘት አይለውጠውም። ወደፊት እንደሚገለጸው በቃል ግጥሞቹ የሚታየው የቃል/የቃላት ለውጦች ግን የይዘት ልውጠት ያስከትላሉ። የይዘት ልውጠቱ በጽሑፍ ከተመዘገበው የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ታሪክ ጋር ሲነጻጸር የፈጸሙትን እንዳልፈጸሙ የሚገልጽ ወይም የሚቃረን ነው። በቃል ለውጥ ምክንያት በቃል ግጥሞቹ የይዘት ልውጠት እንደሚፈጠረው ኹሉ በድርጊት አተራረክ ልውጠትም ይፈጠራል። የተጠቀሱትን ልውጠቶች በማስረጃ ላይ በመመሥረት ለመስረዳት የሚከተሉት የቃል ግጥሞች ተመርምረዋል።

፩) ሺሕ ሐመር ሺሕ[7] ጉራች የሸዋ ፈረስ፤
አንድ ጥርኝ ኾነ[8] ቢዘልቅ ቴዎድሮስ
(ማኅተመ ሥላሴ፣ ፲፱፻፳፩፤ ፻፳፱)።

፪) በያይነቱ ነበር የሸዋ ፈረስ፣
አንድ ጥርኝ ኾነ ቢዘልቅ ቴዎድሮሽ
(ገሪማ፣ ፲፱፻፺፮፤ ፻፫)።

፫) ሺ ዳለች ሺ ቦራ ነበር የሸዋ ፈረስ፣
አንድ ጥርኝ ኾነ ቢቀር ቴዎድሮስ
(ደስታ፣ (፲፱፻፷፪፤ ፫፻፺፪)።

፬) የታጠቅ ፈረሶች ብዙ ነው ሕብራቸው፤
ሌሎች በነሱ ዘንድ ጥርኝ ብቻ ናቸው
(ገሪማ፣ ፲፱፻፺፮፤ ፻፹፮-፻፹፯)።

---

[7] ይኽ ቃል በተጠቀሱት የቃል ግጥሞች በተለያዩ ምእላዶች ቅንጅቶች ተጽፎ የሚነበበው ከምንጩ እንደተገኘው በመጻፉ ነው።

[8] የቃል ግጥሞቹ ይዘቱን ለመግለጽ “ጥርኝ” እና “ኾነ” የሚሉ ቃላትን ተጠቅመዋል። “ጥርኝ” የሚለው ቃል ፍቺ “የእፍኝ ግማሽ፣ በአንድ የውስጥ እጅ ሊያዝ የሚችል መጠን” የሚል ነው (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1993፤ 559)። “ኾነ” የሚለው ቃል ፍቺ ደግሞ “አንድን ዓይነት፣ መጠን፣ መልክ፣ ባህርይ፣ ግብር፣ ሥራ ያዘ” የሚል ነው (አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1993፤ 10)። “ጥርኝ” እና “ኾነ” የሚሉትን ቃላት ሲጣመሩ መጠኑ፣ ዐቅሙ ቀነሰ ማለትን ይገልጻሉ። ከዚኽም የቃል ግጥሞቹ በሠማቸውም፣ በወርቃቸውም ያስተላለፉት ኹለቱን ቃላት በማጣመር መኾኑን መረዳት ይቻላል።

፱) ሺህ ሐመር ሺህ ዳለች ሺህ ቦራ ይሉት የነበረ የሸዋን ፈረስ፣
አንድ ጥርኝ ቀረ ቢዘልቅ ቴዎድሮሽ
(ተክለ ጻድቅ፣ ፲፱፻፹፩፣ 171)።

በተራ ቁጥር ፰ እና ፱ የተጠቀሱት የቃል ግጥሞች ተመሳሳይነትም፣ ልዩነትም ይስተዋላል። ኹለቱም የቃል ግጥሞች በሠማቸው የሸዋ ፈረሶች ብዙ መኾናቸውን፣ የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ፈረስ ግን አንድ ብቻ መኾኑን በተመሳሳይ ይገልጻሉ። በወርቃቸውም በተመሳሳይ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ወደ ሸዋ በዘመቱባቸው ጊዜ ብዙ ቁጥር ኾነው ለጦርነት የተሰለፉት (”ሐመር” እና “ጉራች” መልክ ያላቸው ኹለት ሺሕ ፈረሰኞች) የሸዋ ፈረሰኞች የተከፈተባቸውን ጥቃት የመመከት እና የመከላከል ዐቅማቸው በጣም ዝቅተኛ ኾነ፤ የመዋጋት ዐቅማቸው አንሶ ተገኘ፣ እንደ ቁጥራቸው ብዛት ሳይዋጉ ቀሩ፤ በቀላሉ ተሸነፉ ማለትን ይገልጻሉ። የዚኽ የቃል ግጥም ይዘት በውጤቱ ላይ ያተኮረ በመኾኑ የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን አሸናፊነት አጋኖ፣ የሸዋዎቹን ፈረሰኞች አኮስሶ ይገልጻል። ወደፊት ከሚገለጸው ታሪክ መረዳት እንደሚቻለው ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ወደ ሸዋ ካደረጓቸው ሦስት ዘመቻዎች በመጀመሪያው እና በኹለተኛው ዘመቻ የሸዋ ፈረሰኞች ከፍተኛ መከላከል በማድረጋቸው “በቀላሉ ተሸነፉ” የሚለው ትክክል ነው ለማለት ያስቸግራል። ስለኾነም፣ የቃል ግጥሙ ይዘት የተጋነነ ቢኾንም በመጀመሪያው እና በኹለተኛው የሸዋ ዘመቻ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ያገኙትን የድል ታሪክ አንፀባርቋል ማለት ይቻላል።

በተራ ቁጥር ፰ በተጠቀሰው የቃል ግጥም የሸዋ ፈረሶች “ሐመር” እና “ጉራች” መኾናቸው፣ በተራ ቁጥር ፱ በተጠቀሰው የቃል ግጥም ደግሞ የሸዋ ፈረሶች ብዛት እና መልካቸው “በያይነቱ” በማለት መገለጹ እንደ ልዩነት ሊቆጠር ይችላል። ምክንያቱም “በያይነቱ” የሚለው ከአንድ በላይ የኾነ የቀለም ዓይነት ማለት ስለኾነ ቃል በተራ ቁጥር ፰ የተጠሩትን “ሐመር” እና “ጉራች” የሚሉትን ፈረሶች ለመጥራቱ እርግጠኛ መኾን አለመቻል ነው። ቃሉ በተራ ቁጥር ፰ የተጠሩትን ፈረሶች ጨምሮ ሌሎች መልክ እና ብዛት ያላቸውን ፈረሶች ማለት ሊኾን ይችላል። ከዚኽም ሌላ፣ በተራ ቁጥር ፰ የተጠሩትን ፈረሶች ሳይጨምር ሌሎች ፈረሶችን ማለትን ሊገልጽ ይችላል። ይኽም ኾኖ “በያይነቱ” የሚለው ቃል በቃል ግጥሙ የሚነገረውን ይዘት አላዛባም ወይም እንዲለወጥ አላደረገም። በቃል ግጥሙ የታየው ልውጠት የቅርጽ ብቻ ነው ሊባል ይችላል።

በኹለቱ ተራ ቁጥሮች ከተጠቀሱት የቃል ግጥሞች አንደኛው ከሌላኛው ቀድሞ እንደተዜመ እርግጠኛ ኾኖ መናገር ያስቸግራል። ይኽም ኾኖ በተራ ቁጥር ፰ የተጠቀሰው የቃል ግጥም ቀድሞ እንደተዜመ ለመገመት የሚያስችሉ መረጃዎችን መጥቀስ ይቻላል። ይኸውም አንደኛ፣ በተራ ቁጥር ፰ በተጠቀሰው የቃል ግጥም በመጀመሪያው ሥንኝ የተጠሩት ፈረሶች በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የንግሥና ዘመን የነበረውን በፈረስ የመዋጋት ባህል በማንፀባረቁ ነው። በሸዋ መሳፈንት/መኳንንት እና በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ይመራ በነበረው ጦር መካከል በተደረገው ጦርነት ኹለቱም ወገኖች ለውጊያ ፈረስን ተጠቅመዋል ተብሎ ይታመናል። ኹለቱ ወገኖች በፈረስ ያደረጉትን ውጊያ በዐይን ዐይቶ ወይም በጆሮ ሰምቶ ለውጊያ የተገለገሉባቸውን ፈረሶች መልካቸውን በመጣራት የቃል ግጥሙን ማዜም ተችሎ ይኾናል። ኹለተኛ፣ በቃል ግጥሙ በወርቁ በተገለጸው ይዘት ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ወደ ሸዋ ዘምተው ማስገበራቸውን በትክክል ማንፀባረቁ (የተጋነነ ቢኾንም) ቀድሞ

ለመዜሙ ማስረጃ ሊኾን ይችላል። በተራ ቁጥር ፩ የተጠቀሰውን የቃል ግጥም ሲዜም የሰማ ሰው በሌላ አጋጣሚ አስታውሶ በትክክል ለማዜም ወይም ለመመዝገብ ባለመቻሉ ወይም ኾን ብሎ እንዲሻሻል በመደረጉ በተራ ቁጥር ፪ የተጠቀሰውን የቃል ግጥም አዚሞ ሊኾን ይችላል። ለውጡ የአማርኛውን የቃል ግጥም አሠነኛኘት ባህል መሠረት በማድረግ የተካኼደ ነው።

በተራ ቁጥር ፫ የተጠቀሰው የቃል ግጥም በተራ ቁጥር ፩ እና ፪ ከተጠቀሱት ጋራ በሠሙ በተላለፈው ይዘት ተመሳሳይ ሲኾን በወርቁ ግን ይለያል፤ ይቃረናል። በቃል ግጥሙ የተፈጠረው የይዘት ልውጠት ቀድሞ በተሰማው የቃል ግጥም በሠሙም፣ በወርቁም የገለጸውን ይዘት በትክክል ለማስታወስ ባለመቻል ይመስላል። የቃል ግጥሙን ያዜመው ወይም የመዘገበው ሰው ቀድሞ በሰማው የቃል ግጥም “ጥርኝ” የሚለው መጠሪያ “ኾነ” ከሚለው ቃል ጋር ተጣምሮ ምን ይዘት እንዳስተላለፈ ያስታወሰ አይመስልም። ይኽም በቃል ግጥሙ በወርቁ መገለጽ የሚገባው ይዘት እንዳይተላለፍ ከማድረጉም በላይ በታሪክ የሚታወቀውን እና ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ወደ ሸዋ ዘምተው ማስገበራቸውን አይገልጽም።

በቃል ግጥሙ ወርቅ የተገለጸው ይዘት የተለየ ወይም የተቃረነ ያደረገው በተራ ቁጥር ፫ በተጠቀሰው የቃል ግጥም የተፈጠረው የቃል ለውጥ ነው። ይኸውም በተራ ቁጥር ፩ በተጠቀሰው የቃል ግጥም በኹለተኛው ሥንኝ የሚነበበው “ቢዘልቅ” የሚለው ቃል በተራ ቁጥር ፫ በተጠቀሰው የቃል ግጥም “ቢቀር” በሚል ቃል መተካቱ ነው። “ቢዘልቅ” የሚለው መምጣትን፣ “ቢቀር” የሚለው ደግሞ አለመምጣትን የሚገልጽ በመኾኑ የቃል ለውጡ በቃል ግጥሙ በወርቁ በተገለጸው ይዘት ልውጠት እንዲፈጠር አድርጓል። የቃል ግጥሙ በወርቁ “የሸዋ ፈረሰኞች ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ወደ ሸዋ ሳይዘምቱባቸው፣ ሳይመጡባቸው ከዐቅምም፣ ከግምትም በታች ተዋግተው በቀላሉ ተሸነፉ” ማለትን ይገልጻል። ይኽ አገላለጽ ተጠየቃዊ ስሕተት ይነበብበታል፤ የታሪክ ተፋልሶም ተነግሮበታል። ስሕተቱም፣ አንደኛ፣ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ወደ ሸዋ ሳይዘምቱ እና ከሸዋ ፈረሰኞች ጋር ግንባር ለግንባር ሳይገናኙ “የውጊያ ዐቅማቸው አንሶ፣ ኮስሶ ታየ”፤ “ከዐቅም በታች ተዋጉ” በማለት መግለጽ ተጠየቃዊ አለመኾኑ ነው። ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ወደ ሸዋ ሳይዘምቱ እና ከሸዋ ፈረሰኞች ጋራ ጦርነት ሳይገጥሙ የሸዋ ፈረሰኞች መዋጋት በሚገባቸው ልክ ወይም መጠን ባለመዋጋታቸው በእሳቸው ተሸነፉ ማለት አይቻልም። በቃል ግጥሙ “የታሪክ ተፋልሶ ተነግሯል” ማለት የተቻለው “ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ወደ ሸዋ ሳይመጡ (ሳይዘምቱ) ቀሩ” የሚለው አገላለጽ (ይዘት) ወደ ሸዋ ዘምተው ማስገበራቸውን እና በተለያዩ ጸሓፍት ተመዝግቦ የሚገኘውን ታሪካቸውን ይቃረናል። በታሪክ እንደሚታወቀው ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ወደ ሸዋ ሦስት ጊዜ ዘምተው በመጀመሪያዎቹ ኹለት ዘመቻዎች ከሸዋ መሳፍንት እና መኳንንት ጋራ ከባድ ጦርነት አድርገዋል (ታሪኩ በአጭሩ ወደፊት ይቀርባል)።

ልውጠቱ የተፈጠረው በተራ ቁጥር ፫ የተጠቀሰውን የቃል ግጥም ያዜመው ወይም የመዘገበው ሰው ቀድሞ የሰማውን የቃል ግጥም (በተራ ቁጥር ፩ ወይም ፪ የተጠቀሰውን) በትክክል ማስታውስ ባለመቻሉ ይመስላል። የቃል ግጥሙን ያዜመው ወይም የመዘገበው ሰው ያስታወሰው ቀድሞ ከተዜመው የቃል ግጥም በሠሙ የተነገረውን ይዘት ብቻ ነው። በወርቁ የተነገረውን እና ዳግማዊ ዐፄ ትዎድሮስ ወደ ሸዋ ዘምተው ከሸዋ ፈረሰኞች ጋር መዋጋታቸውን የሚገልጸውን ታሪክ (ይዘት)

ግን አላስታወሰም። ያላስታወሰውን የቃል ግጥሙን ኹለተኛውን ሥንኝ የተካውም የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን ታሪክ በማይገልጽ ቃል ነው። ይዘቱ በታሪክ ከሚታወቀው የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ታሪክ መቃረኑ የቃል ግጥሙን ያዜመው ወይም የመዘገበው ሰው "ኾን ብሎ አሻሽሎታል" እንዳይባል ያደርጋል።

በተራ ቁጥር ፬ በተጠቀሰው የቃል ግጥም ኹለተኛው ሥንኝ ከሌሎቹ ማለትም በተራ ቁጥር ፩፣ ፪ እና ፫ ከተጠቀሱት የቃል ግጥሞች የተለየ የቃል ለውጥ ይነበብበታል። ለውጡም "ኾነ" የሚለው ቃል በተራ ቁጥር ፬ በተጠቀሰው የቃል ግጥም "ቀረ" በሚል ቃል መተካቱ ነው። የቃል ለውጡም "አንድ ጥርኝ ኾነ" (አነሰ) የሚልን ይዘት "አንድ ጥርኝ ቀረ" (አልሸሸም፣ ቆመ) በማለት ይገልጻል። ይኸም የቃል ግጥሙ ይዘት በሠሙ ሦስት ሺሕ "ሐመር" ፣ "ዳለች" እና "ቦራ" የሸዋ ፈረሶች ሲሸሹ አንድ ጥርኝ ብቻ ቀረ ማለትን ይገልጻል። የቃል ግጥሙ በወርቁ የተነገረው ይዘት ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ወደ ሸዋ በመጡበት (በዘመቱበት) ጊዜ በ"ሐመር"፣ በ"ዳለች" እና በ"ቦራ" ፈረሶች ይዋጉ የነበሩት ሦስት ሺሕ የሸዋ ተዋጊዎች ኹሉም ሲሸሹ በጥርኝ ፈረስ ይዋጋ የነበረው ብቻ ሳይሸሽ ቀረ፤ አንድ ፈረሰኛ ብቻ ሳይሸሽ ተገኘ፣ ለመመከት፣ ለመፋለም ቆረጠ፣ ተዘጋጅቶ ጠበቀ፣ ብቻውን ለፍልሚያ ተዘጋጀ ማለትን ይገልጻል።

በቃል ግጥሞቹ የፈረሶች መልክ እና ቁጥር ተጨምሮ ወይም ተቀንሶ ወይም ተለውጦ ተጠርቷል። ይኸ የተፈጠረው ቀድሞ የተሰማን የቃል ግጥም አስታውሶ ማዜም ወይም መመዝገብ ባለመቻሉ ወይም ኾን ብሎ በማሻሻል ሊኾን ይችላል። ይኽን ማድረግም የቃል ግጥሙ የልውጠት ባሕርይ ይፈቅዳል። ፈረሶች በተለያዩ መልኮች የተጠሩት ቀድመው የሰሙትን ማስታወስ ያልቻሉ ሰዎች በባህሉ ፈረስ የሚጠራበትን አጠቃላይ ዕውቀት መሠረት በማድረግ በመተካታቸው ወይም ኾን ብለው በማሻሻላቸው ሊኾን ይቻላል። የፈረሶቹ መልክ እና ቁጥር ተጨምሮ ወይም ተቀንሶ ወይም ተለውጦ መነገሩ በቃል ግጥሞቹ ይዘት ላይ ተፅዕኖ አላስከተለም፤ አንደኛው ከሌላኛው ቀድሞ ለመዜሙ ማስረጃ አይኾንም።

በተራ ቁጥር ፩ እና ፭ በተጠቀሱት የቃል ግጥሞች ጊዜ አመልካች ቃላት ወይም ሐረጋት አይነበቡም። በተራ ቁጥር ፪፣ ፫ እና ፬ በተጠቀሱት የቃል ግጥሞች ግን በተመሳሳይ "ነበር" እና "ይሉት የነበረ" የሚሉ ጊዜ አመልካች ሐረጎች በቅደም ተከተል ይነበባሉ። እነዚኽ ጊዜ አመልካች ሐረጎች አንድ የተወሰነ ዓመተ ምሕረትን ወይም ዘመንን መግለጽ ባለመቻላቸው መቼ የነበሩትን የሸዋ ፈረሶች እንደገለጹ መረዳት አይቻልም። ይኹን እንጂ፣ ጊዜው መቼ እንደ ነበር ማወቅ የተቻለው በዐምስቱም ተራ ቁጥሮች በተጠቀሱት የቃል ግጥሞች የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ/የታጠቅ ስም መጠራት ነው።

በቃል ግጥሞቹ መካከል ሌላም ተመሳሳይነት እና ልዩነት ይታያል። በተራ ቁጥር ፩ በተጠቀሰው የቃል ግጥም የተጠሩት "ሐመር" እና "ጉራች"፣ በተራ ቁጥር ፪ "በያይነቱ"፣ እንዲኹም በተራ ቁጥር ፭ "ኅብራቸው" በሚሉ ቃላት ተተክተዋል። እነዚኹ በተራ ቁጥር ፩ የተጠሩት ፈረሶች በተራ ቁጥር ፫ በተጠቀሰው የቃል ግጥም "ዳለች" እና "ቦራ" በሚሉ ፈረሶች ተተክተዋል። በተራ ቁጥር ፩ ከተጠሩት ፈረሶች መካከል በተራ ቁጥር ፬ የተጠራው "ሐመር" የሚለው ብቻ ነው። በተራ ቁጥር

፫ በተጠቀሰው የቃል ግጥም "ዳለች" እና "ቦራ" በማለት የተጠሩት የሸዋ ፈረሶች፣ በተራ ቁጥር ፬ በተጠቀሰው የቃል ግጥምም በተመሳሳይ ተጠርተዋል። በተራ ቁጥር ፬ በተጠቀሰው የቃል ግጥ" ሐመር"፣ "ዳለች" እና "ቦራ" ሲሸሹ "ጥርኝ" አለመሸሹ መገለጹ የሸዋን ፈረሶች ቁጥር በሌሎች የቃል ግጥሞች ከተገለጹት ከፍ ያደርገዋል። በቃል ግጥሞቹ "ጥርኝ" የሚለው መጠሪያ ከሌሎቹ የፈረስ መጠሪያዎች በተለየ ኹለት ዓይነት አገልግሎት እንዲኖረው ተደርጓል። ይኸውም ከተራ ቁጥር ፭ እስከ ተራ ቁጥር ፯ በተጠቀሱት የቃል ግጥሞች መጠሪያው በተለያዩ ዐውዶች በፈረስ መጠሪያነት እና በመጠን መግለጫነት አገለግሏል።

በተራ ቁጥር ፯ የተመዘገበው የቃል ግጥም በቃላት አጠቃቀሙ፣ በሥንኝ አደራደር እና በይዘት አገላለጹ ከሌሎቹ የቃል ግጥሞች ይለያል።[9] በሌሎች ተራ ቁጥሮች በተጠቀሱት የቃል ግጥሞች የሸዋ ፈረሶች መልካቸው ሲገለጽ (በያይነቱ በማለት ከተገለጹት በስተቀር) በተራ ቁጥር ፯ በተጠቀሰው የቃል ግጥም ደግሞ የታጠቅ ፈረሶች "ብዙ ነው ኅብራቸው" በሚል ተገልጸዋል። "ኅብራቸው" የሚለው ቃል ዐውዳዊ ፍቺ የልዩ ልዩ ቀለማት ቅንብር፣ ቅንጅት እና አንድነት ማለትን ይገልጻል። "የልዩ ልዩ ቀለማት ቅንብር" የሚለውም የታጠቅ ፈረሶች መልክ የተለያየ መኾኑን፣ "ኅብራቸው ብዙ ነው" መባሉም ብዙ መኾናቸውን ይገልጻል። በዚኹ የቃል ግጥም ኹለተኛው ሥንኝ "ሌሎች" በማለት የተጠሩት ፈረሶች መልካቸውም፣የማን መኾናቸውም አልተገለጸም። የቃል ግጥሙ በሠሙ "ሌሎች" በማለት የተጠሩት ፈረሶች ብዙ ቁጥር ካላቸው የታጠቅ ፈረሶች ጋር ሲነጻጸሩ "ቁጥራቸው ከዚኽ ግባ የሚባል አይደለም፤ ትንሽ ናቸው" ማለትን ይገልጻል። በወርቁ የተነገረው ይዘት ደግሞ የታጠቅ ተዋጊ ፈረሰኞች "ሌሎች" በማለት የተጠሩትን ፈረሰኞች በቀላሉ ድል አድርገዋል፣ አሸንፈዋል የሚል ነው። በወርቁ እንደተገለጸው የታጠቅ ፈረሰኞች "ሌሎች" በማለት የተጠሩትን ፈረሰኞች ያሸነፉት በቁጥር በመብለጣቸው ነው። "ሌሎች" ፈረሰኞችም የተሸነፉት በቁጥር በማነሣቸው እንጂ ከዐቅም በታች በመዋጋታቸው፣ በጀግንነት ባለመመከታቸው አይደለም። በቃል ግጥሙ ታጠቅ የተሞገሱት ብዙ ጦር በማደራጀታቸው እና በጠላቶቻቸው ላይ የበላይነት በማግኘታቸው ነው። ጠላቶቻቸውን ያሸነፉት በውጊያ ብቃታቸው እና በጀግንነታቸው መኾኑ አልተገለጸም። የተሸናፊዎቹ ድክመት ተደርጎ የተገለጸው ብዛት ያለውን የታጠቅን ጦር ለመመከት የሚችል ተመጣጣኝ ቁጥር ያለው ፈረሰኛ ለማደራጀት አለመቻላቸው ነው። የታጠቅ ፈረሰኞች ከእነሱ በቁጥር የሚያንሱትን ፈረሰኞች አሸንፈዋል የሚለው አገላለጽ ከነገሡ በኋላ በተቀናቃኞቻቸው ላይ የነበራቸውን የውጊያ የበላይነት ያንፀባርቃል።

በተራ ቁጥር ፬ በተጠቀሰው የቃል ግጥም ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ወደ ሸዋ እንዳልዘመቱ እና እንዳላስገበሩ የሚገልጸው ይዘት በታሪክ ከተመዘገበው ታሪካቸው ይቃረናል። መጀመሪያ ወደ ሸዋ ባካኼዱት ዘመቻ የሸዋ መሳፍንት እና መኳንንት የተሸነፉት ከፍተኛ የመከላከል ጦርነት አድርገው ነው። ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ መጀመሪያ ወደ ሸዋ ያደረጉት ዘመቻም "አምስት ወር ያህል የፈጀ" ነበር (ባሕሩ ዘውዴ፣ ፪ሺህ፤ 31)። በዘመቻውም ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ሸዋን ይገዙ ከነበሩት ከኃይለ መለኮት እና በሥራቸው ከነበሩት መሳፍንት እና መኳንንት ጋራ ተዋግተዋል (ሥርግው

9 የቃል ግጥሙ ከተጠቀሱት ሌሎች የቃል ግጥሞች የሚያመሳስለው መሠረት ባደረገው ይዘት (የታጠቅ ታሪክ)፣ በሥንኞቹ መንቶነት፣ አመጣጠን እና ፈረሶች በተመሳሳይ እና በልዩነት መጠራቱ ነው።

ሐብለ ሥላሴ፣ 2000፤ 138-140)። ኃይለ መለኮት በሕመም ምክንያት ከሞቱ በኋላም የሸዋ መኳንንት ተመካክረው አቶ ናደውን ሞግዚት አደርገው ሕፃኑ ምኒልክ የአባታቸውን ዐልጋ እንዲረከቡ አደረጉ። ከዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ጥቃት ለማምለጥም ምኒልክን ይዘው ከአንኮበር በስተ ደቡብ ቡልጋ ውስጥ ወደሚገኘው ገበሬ ሸንኅ ቀበሌ ሸሹ። ሽሽታቸውን በመቀጠልም ከሰምን ተሻግረው አረርቲ ሰፈሩ። በዚኽም ቦታ ሸዋዎች ጠንካራ ውጊያ አድርገው ራስ እንግዳ የተባሉትን የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ጦር መሪ አሸነፉ። ከሸዋዎች በኩልም አቶ ሽሽጉ እና አቶ አብቱ ሲሞቱ በዛብህ የተባሉት ደግሞ ተማረኩ። የሸዋ ተዋጊዎች ያሸነፉት የራስ እንግዳን እንጂ የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን ጦር አለመኾኑን ከምርኮኞቹ አንዱ ሲነግራቸው ወደ ምንጃር ሸሹ። መሸሻቸው እንዳላዋጣቸው የተገነዘቡት የሸዋ የጦር አለቆች ሕፃኑን ምኒልክን ይዘው ለዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ እጅ ሰጡ። ከዚኽ በኋላ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስም ለሸዋ አስተዳዳሪ እና የጦር አበጋዝ ሾመው ምኒልክን ይዘው በጃርሶ በኩል ዐባይን ተሻግረው በደጀን፣ ከዚያም በባሕር ዳር አድርገው ወደ በጌምድር ተመለሱ (ሥርግው ሐብለ ሥላሴ፣ 2000)።

ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ለኹለተኛ ጊዜ ወደ ሸዋ የዘመቱት የንጉሥ ኃይለ መለኮት ወንድም አቤቶ ሰይፈ ሚካኤል[10] ሣህለ ሥላሴ በሸዋ በተሾሙት በአፈ ንጉሥ አቦዬና በአበጋዝ በዛብኽ ላይ ዐምፀው አንኮበርን ወርረው ሥልጣን በያዙበት ጊዜ ነው። ይኽ ድርጊት የተነገራቸው ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ በ፲፰፻፶፪ ዓ. ም. ከወሎ ገሥግሠው አንኮበር ላይ በመሸገው አቤቶ ሰይፈ ሚካኤል ላይ ጥቃት ከፈቱ። "በዚያም ቀን እስከ ማታ ድረስ ጥኑ ውጊያ ተዋጉ። ያጼ ቴዎድሮስም ሰው ቁጥር የሌለው ብዙ ሰው አለቀ። አጼ ቴዎድሮስም የጦርነቱን መጠንከር አይተው እነዚህ ሰዎች ቀድሞ ግሼ ላይ አግኝተውን ቢሆን ሸዋ አያስገቡንም ኑረዋል ብለው አደነቁ" (ገብረ ሥላሴ፣ ፲፱፻፶፬፤ ፶፫)። አቤቶ ሰይፈ ሚካኤል የተከፈተባቸውን ጥቃት በሚገባ በተቋቋሙበት እና ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ተስፋ በቆረጡበት ሰዓት አንድ ወታደራቸው ተማርኮ አቤቶ ሰይፈ ሚካኤል ፊት ይቀርባል። አቤቶ ሰይፈ ሚካኤልም ተማራኪውን የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን ጦር ማን እንደሚመራው ይጠይቁታል። ጦሩን የሚመሩት ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ መኾናቸውን ይነግራቸዋል። ይኽን የሰሙት አቤቶ ሰይፈ ሚካኤል ለመሸሽ ይወስናሉ። ውሳኔአቸውን ለወታደሮቻቸው ነግረው "እሺ" ያሉትን አስከትለው ወደ ጨርጨር ይሸሻሉ። እንደ ሸሹም ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ አንኮበርን ተቆጣጠሩ (ገብረ ሥላሴ፣ ፲፱፻፶፬)። ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ በአንኮበር ስለ ኣጋጣማቸው ከባድ ጦርነት በኋላ ግብር ላይ ሲያወሩ "በዕድሜዬ ሦስት የጠነከረ ጦርነት ገጠመኝ። አንድ አንኮበር ካቶ ሰይፉ ጋራ፣ ሁለተኛ ከጋረድ ጋራ፣ ሦስተኛ እንጃባራ [እንጅባራ]። ከእነዚህ ከሦስቱ በቀር ሌላ ጦርነት አላውቅም" ማለታቸውን ሥርግው ሐብለ ሥላሴ (2000፤ 150) ገልጸዋል። በተጨማሪም ሥርግው ሐብለ ሥላሴ (2000፤) የዘመኑ ታሪክ ጸሓፊ ወልደ ማርያም ስለ አንኮበር ጦርነት የዘገቡትን "የዚያን ቀን ይህ የተማረከው የንጉሡን ወገን ወሬ ባይነግር የመጣው ጦር ለዘር ባልተመለሰም ነበር። ንጉሡም

---

[10] ይኽ መጠሪያ በገብረ ሥላሴ (፲፱፻፶፱፤ ፶፫) "አቶ ሰይፉ" እና "አቤቶ ሰይፉ" ፣ በተክለ ጻድቅ መኩሪያ (፳፻፤ ፲፰) "አቤቶ ሰይፉ"፣ በሥርግው ሐብለ ሥላሴ (2000፤ 149) "ሰይፈ ሚካኤል"፣ "ሰይፉ"፣ "አቶ ሰይፉ" እና "አቤቶ ሰይፉ"፤ በባሕሩ ዘውዴ (፪ሺህ፤ 31) "ሠይፉ ሣህለ ሥላሴ" በማለት ተጠርቷል። አቤቶ የሚለው የስም ቅጽል ጌታ፣ ጌታው ማለት ነው። ይኽንን የክብር መጠሪያ የሸዋ መሳፍንት አቤቶ ሣህለ ሥላሴ፣ አቤቶ ዳርጌ፣ አቤቶ ሰይፉ እየተባለ ይጠሩበት ነበር (ደስታ፣ ፲፱፻፹፪፤ ፸፰) ። ስለኾነም ሰይፈ ሚካኤል ከሸዋ መሳፍንት አንዱ ስለ ነበሩ በዚኽ ጥናት መጠሪያቸውን በወጥነት አቤቶ ሰይፈ ሚካኤል ለማለት ተችሏል።

የዚኽን ጦርነት በአቤቶ ሰይፉ ቢያዩ ‹እንደነዚህ ያሉት በፊት ተገኝተው ቢሆን ሸዋን አላያትም ነበር። የወታደር ሞያ በአንኮበር ብቻ ይቆጠር› አለ" (ገጽ 150) በማለት ጠቅሰው ገብረ ሥላሴ የዘገቡትን ደግፈዋል። ይኽም የሸዋ ጦር ከዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ጋራ ምን ያኽል ከባድ ውጊያ እንዳደረገ ያስረዳል።

ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ለሦስተኛ ጊዜ ወደ ሸዋ የዘመቱት በ፲፰፻፶፯ ዓ. ም. ነበር (ሥርግው ሐብለ ሥላሴ፣ 2000፤ 151)። የዘመቱትም "በዛብህ ካበጋዝነት ወጥቶ እነግሣለሁ ብሎ በተነሣ ጊዜ" ነው (ገብረ ሥላሴ፣ ፲፱፻፵፬፤ ፶፬)። በዚኽን ጊዜ በዛብኽ አፍቀራ ዐምባ ገብቶ ለመያዝ በማስቸገሩ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ማጥቃት ሳይችሉ ቀሩ። ረዘም ያለ ጊዜ በሸዋ ለመቆየት የማያስችል የባሰ ችግር ስለ ነበረባቸው ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የፈለጉትን ሳያሳኩ ነገሩን አንጠልጥለው ወደ በጌምድር ተመለሱ (ሥርግው ሐብለ ሥላሴ፣ 2000፤ Crummey, 1971)። ገብረ ሥላሴም (፲፱፻፵፬፤ ፶፬) "መንዝ ላይ ሰፍረው ሳይሆንልዎ ቀርተው ተመልሰው ወደ መቅደላ ሔዱ" በማለት ይገልጻሉ (አጽንኦት የታከለ)። ገብረ ሥላሴ ከገለጹት መረዳት እንደሚቻለው ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ለሦስተኛ ጊዜ ወደ ሸዋ በዘመቱበት ጊዜ ምንም ዓይነት ውጊያ አላደረጉም። ይኽም ውጊያ ሳይደረግ "የሸዋ ጦር ከዐቅም በታች ተዋግቶ በዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ተሸነፈ" በማለት መግለጽ በታሪክ ማስረጃ የማይደገፍ ነው። ይልቁንም ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ለሦስተኛ ጊዜ ወደ ሸዋ ዘምተው ሳይዋጉ መመለሳቸው ለውጊያ ዝግጁ የነበረውን የሸዋ ጦር ፈታኝ ነገር እንዳልገጠመው ያስረዳል።

ከተጠቀሱት ታሪካዊ ድርጊቶች መገንዘብ እንደሚቻለው የሸዋ ፈረሰኞች "ከዐቅም በታች ተዋግተው ተሸነፉ" በማለት በተራ ቁጥር ፭፣ እና ፪ በተጠቀሱት የቃል ግጥሞች የተገለጸው ትክክለኛውን ታሪካዊ እውነታ አያንፀባርቅም። የቃል ግጥሞቹ የሸዋን መሳፍንት እና መኳንንት ሽንፈት የጅግንነት እና የመስዋዕትነት ጉደለት አድርገው መግለጻቸው ታሪካዊ እውነታውን አያንፀባርቅም። የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ጦር በመጀመሪያውም፣ በኹለተኛውም የሸዋ ዘመቻ በከፍተኛ ደረጃ መክቶ እንጂ በቃል ግጥሞቹ እንደ ተገለጸው ከዐቅም በታች ተዋግቶ በቀላሉ አልተሸነፈም። ለሦስተኛ ጊዜ ያደረጉት ዘመቻም ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ በመመለሳቸው የሸዋ ጦር ለፊልሚያ እንደተዘጋጀ የቀረ ነው።

በተራ ቁጥር ፭፣ ፫ እና ፬ በተጠቀሱት የቃል ግጥሞች የተጠሩት ፈረሶች ብዛት እና መልክ ተመሳሳይም፣ የተለያየም ነው። የተለያየ መልክ ያላቸው ፈረሶች መጠራት እና ብዛታቸው መለያየቱ በቃል ግጥሞቹ የቅርጽ ልውጠት እንዲፈጠር አድርጓል። በተራ ቁጥር ፪ በተጠቀሰው የቃል ግጥም የሸዋ ፈረሶች ብዛት እና መልክ አልተገለጸም። "በያይነቱ" የሚለው ቃልም ፈረሶቹ የተለያዩ መልኮች እንዳላቸው እንጂ፣ ሐመር፣ ዳለች፣ ጉራች ወዘተ. በማለት መልካቸውን አይጠራም። በተራ ቁጥር ፫ በተጠቀሰው የቃል ግጥም ደግሞ የታጠቅ ፈረሶችን "ኀብራቸው" በማለት ልዩ ልዩ መልክ እንደ አላቸው ሲገልጽ የሸዋ ፈረሶች ግን አልተጠሩም። በቃል ግጥሙ ለየታጠቅ ፈረሶች ብዙ መኾናቸውን እንጂ ቁጥራቸው ስንት እንደኾኑ አይገልጽም። ይኽም የቃል ግጥሙን የሸዋን ፈረሶች መልክ ነግረው ብዛታቸውን ከገለጹት ሌሎች የቃል ግጥሞች የተለወጠ አድርጎታል። በቃል ግጥሞች የሚታዩ የቃላት ለውጦች የይዘትም ልውጠት አስከትለዋል። በተራ ቁጥር ፫ በተጠቀሰው የቃል

ግጥም የተገለጸው ይዘት ከሚታወቀው እና በጽሑፍ ከተመዘገበው የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ታሪክ ጋራ የሚቃረን ወይም የፈጸሙትን እንዳልፈጸሙ የሚገልጽ ነው። በተራ ቁጥር ፫ በተጠቀሰው የቃል ግጥሙ የተገለጸው ይዘትም ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ወደ ሸዋ መዝመታቸውንና መዋጋታቸውን በግልጽ አይነግርም።

ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ለኹለተኛ ጊዜ ወደ ሸዋ በዘመቱ ጊዜ ከአቤቶ ሰይፈ ሚካኤል ጎን ተሰልፈው ከወጓቸው መካከል የማረኳቸውን ባለወግ አስጠርተው ቀኝ እጃቸውንና ግራ እግራቸውን በማስቆረጥ መቅጣታቸው በውጊያው የደረሰባቸውን ጉዳት ለመበቀል የፈጸሙት ተደርጎ ይቆጠራል። ይኽም ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ አጋጥሟቸው የነበረውን ጦርነት ከባድነት ይጠቁማል።

በተለያዩ ጸሓፍት በተለያየ ቅርጾች የተመዘገቡት የቃል ግጥሞች የሚከተሉት ናቸው።

፩) ዐፄ ቴዎድሮስ ምነው ተዋረዱ፣
የሸዋን ሰው ሁሉ እጅ ነሥተውት ሔዱ
(ገብረ ሥላሴ፣ ፲፱፻፶፱፤ ፶፫)።

፪) ዐፄ ቴዎድሮስ እጅግ ተዋረዱ፤
የሸዋን መኳንንት እጅ ነሥተው ኼዱ
(ማኅተመ ሥላሴ፣ ፲፱፻፷፩ ፤ ፪፻፴፩)።

፫) ዐፄ ቴዎድሮስ እጅግ ተዋረዱ፣
የሸዋን ሰው ሁሉ እጅ ነሥተውት ሔዱ
(ሥርግው ሐብለ ሥላሴ፣ 2000፤ 150)
(ዊዳሌ፣ 1897፤ 21፤ ተክለ ጻድቅ፣፲፱፻፹፩፤ 197)።

ከዚኽ በላይ በተጠቀሱት የቃል ግጥሞች የተገለጸውን ይዘት ተመሳሳይነት እና ልዩነት እንደሚከተለው ቀርቧል። በተራ ቁጥር ፩ የተጠቀሰው የቃል ግጥም የመጀመሪያው ሥንኝ የሚገኘው "ምነው" የሚለው ቃል "ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ፣ ንጉሥ እና የተከበሩ መኾናቸው እየታወቀ ክብራችውን ዘንግተው ወይም ትተው ለትንሹም፣ ለትልቁም፣ ለሴቱም ለወንዱም ጎንበስ ብለው ሰላምታ ማቅረባቸው፣ መስጠታቸው ራሳቸውን አዋርደዋል" የሚል ይዘት ያስተላልፋል። ይዘቱም እሳቸው ባሉበት ወይም በሚያልፉበት ቦታ የተገኘ ሰው ኹሉ ለክብራቸው ጎንበስ ብሎ እጅ መንሣት ሲገባው በተቃራኒው እሳቸው ለሸዋ ሕዝብ ንጉሥ በማይፈጽመው ባልተለመደ መንገድ ሰላምታ ያቀርባሉ። ሰላምታ ያቀረቡበት መንገድ ግራ የተጋባ ሰው ራሱን ወይም በአጠገቡ ያለን ሰው "ለምን" እና "በምን ምክንያት" የተጠቀሰውን ዓይነት ሰላምታ እንደ ሰጡ ለማወቅ በመጓጓት ይጠይቃል። በተራ ቁጥር ፪ በተጠቀሰው የቃል ግጥም "ምነው" የሚለውን የጥያቄ ቃል "እጅግ" በሚል ተተክቷል። ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ለኹሉም ሰው እጅ በመንሣት ሰላምታ ማቅረባቸው በከፍተኛ ደረጃ መዋረዳቸው "እጅግ" በሚለው መጣኝ ምእላድ ተገልጿል። በተራ ቁጥር ፩ እና ፪ በተጠቀሱት የቃል ግጥሞች ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ እጅ በመንሣት ሰላምታ ያቀረቡት ለማንኛውም የሸዋ ሰው ሲኾን በተራ ቁጥር ፫ በተጠቀሰው የቃል ግጥም ደግሞ ለሸዋ መኳንንት ብቻ መኾኑ ተገልጿል። ሦስቱም የቃል ግጥሞች በሠማቸው ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ከእሳቸው በማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ደረጃቸው ለሚያንሱት በሸዋ ለሚገኙ ኹሉም ሰዎች/መኳንንት ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ሰላምታ በመስጠታቸው (በማቅረባቸው) የደረሰባቸው

ውርደት ከፍተኛ መኾኑን ይገልጻሉ። በሦስቱም የቃል ግጥሞች በወርቃቸው የተነገረው ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ወደ ሸዋ ዘምተው የሰዎችን እጅ ቆርጠዋል የሚል ነው። በተራ ቁጥር ፩ እና ፪ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ እጅ የቆረጡት የኹሉንም የሸዋ ሰዎች መኾኑ ሲገለጽ፣ በተራ ቁጥር ፫ በተጠቀሰው የቃል ግጥም ደግሞ እጅ የቆረጡት የሸዋን መኳንንት ብቻ ነው። ይኹን እንጂ፣ ገብረ ሥላሴ (፲፱፻፶፬፤ ፶፫) ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ አካል በማስቆረጥ የቀጡት ኹሉንም የሸዋ ሰዎች ወይም መኳንንት አይደለም። ቅጣታቸውም እጅ በማስቆረጥ ብቻ የተወሰነ አልነበረም። ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ቀኝ እጅ እና ግራ እግር በማስቆረጥ የቀጧቸው ከአቤቶ ሰይፈ ሚካኤል ጎን ተሰልፈው አንኮበር ላይ የወጓቸውን እና በወታደሮቻቸው ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሱትን እና የማረኳቸውን ነው። ሥርግው ሐብለ ሥላሴ (2000፤ 149) በበኩላቸው ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የማረኳቸውን እጅና እግራቸውን ከማስቆረጣቸው በተጨማሪ ካህናትንም ማስገደላቸውን ገልጸዋል። የአቤቶ ሰይፈ ሚካኤል ተዋጊዎች በነበሩት ምርኮኞች ላይ እና በካህናት ላይ ቅጣት የመፈጸማቸው ምክንያት በዐፄ ቴዎድሮስ ጦር ላይ ከፍተኛ ጉዳት በመድረሱ እና በመበሳጨታቸው ነው ተብሎ ይታመናል። ይኸም "የሸዋ ጦር ከዐቅም በታች ተዋግቶ ተሸነፈ" በማለት በቃል ግጥሙ የተነገረው ይዘት ትክክል እንዳልኾነ እና ከታሪኩ ጋር አለመጣጣሙን መገንዘብ ይቻላል። የቃል ግጥሞቹን በየሥራቸው የመዘገቡ ሰዎች በማን እንደተዜሙ የዘገቡት ልዩነት ባለው መንገድ ነው። ገብረ ሥላሴ (፲፱፻፶፬፤ ፶፫) እና ተክለጻድቅ (፲፱፻፹፩፤ 197) የቃል ግጥሙን ያዜመችው ማንነቷ ያልተገለጸ አልቃሽ መኾኗን፣ ማኅተመ ሥላሴ (፲፱፻፷፩ ፤ ፪፻፴፩) ደግሞ "ባሏ የሞተባት የሸዋ ሴት ያለቀሰችው" መኾኑን ገልጸዋል። ሥርግው ሐብለ ሥላሴ (2000፤ 149) በበኩላቸው "የዚህን ጊዜ እንዲህ ተባለ" በማለት የለቅሶ ግጥሙን ይጠቅሳሉ። እሳቸውም የለቅሶ ግጥሙ በአካባቢው መዜሙን እንጂ በማን እንደተዜመ አልገለጹም። ከዚኽም በተጠቀሱት የቃል ግጥሞች የቅርጽም፣ የይዘትም ልውጠት መኖሩን መገንዘብ ይቻላል።

6) *መደምደሚያ*

ለዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የተዜሙ የቃል ግጥሞች የተለዋወጡት በጸሐፍቱ ከመመዝገባቸው በፊትም፣ በኋላም ነው ተብሎ ይታመናል። በጸሐፍቱ ከመመዝገባቸው በፊት ተለዋውጠዋል ማለት የተቻለው ንድፈሐሳባዊ መላምቶችን መሠረት በማድረግ ነው። ንድፈሐሳባዊ መላምቶቹም፡- በአንድ አጋጣሚ ላይ የተዜሙ ቃል ግጥሞችን ሙሉ በሙሉ ለማስታወስ ባለመቻሉ ያማርኛውን ቋንቋ አወቃቀር መሠረት በማድረግ የጎደለን ቃል፣ ሐረግ ወይም ሥንኝ ሞልቶ በማቅረብ ኺደት በቃል ግጥሞቹ ላይ ልውጠት ተከስቶ ሊኾን ይችላል። አንድም፣ በአንድ አጋጣሚ ላይ የተዜሙ የቃል ግጥሞች በተለያዩ አጋጣሚዎች ሲዜሙ ከአጋጣሚዎቹና ከተሳታፊዎቹ ማንነት ጋራ እንዲጣጣሙ ለማድረግ ኾን ብሎ በማሻሻል ልውጠት እንዲፈጠር ስለተደረገ ሊኾን ይችላል። አንድም፣ ጸሓፍቱ ስለ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ሲዜሙ ወይም ሲነገሩ የሰሟቸውን የቃል ግጥሞች በትክክል አስታውሰው መመዝገብ ስለአልቻሉ ሊኾን ይችላል። አንድም፣ ጸሓፍቱ የተለዋውጡ የቃል ግጥሞችን ከተለያዩ ሰዎች ሰምተው ስለመዝገቡ ሊኾን ይችላል። በተጠቀሱት እና በሌሎችም ንድፈሐሳባዊ መላምቶች ለዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የተዜሙ የቃል ግጥሞች በተለያዩ ጸሓፍት ከመመዝገባቸው በፊት በተለያዩ አጋጣሚዎች እየተለወጡ እና እየተሻሻሉ ለትውልድ ተላልፈዋል

ተብሎ ይታመናል። ይኸም የቃል ግጥሞቹ መጀመሪያ በተደረሱበት ቅርጽ እና ይዘት ለትውልድ አልተላለፉም ማለት ነው።

የቃል ግጥሞቹ በተለያዩ ጸሓፍት ከተመዘገቡ በኋላም እየተለዋወጡ መተላለፋቸውን በዚኽ ጥናት ለማረጋገጥ ተችሏል። ለውጡም፣ አንደኛ፣ ኹለት ጸሓፍት ከአንድ ምንጭ ቀድተው በየራሳቸው ሥራ ውስጥ ሲመዘግቡ ኹለቱም ወይም አንደኛቸው ለውጠው በመመዝገባቸው የተፈጠረ ነው። ለውጡ አንደኛቸው ወይም ኹለቱም በትክክል መገልበጥ ባለመቻላቸው የተፈጠረ ነው።ኹለተኛ፣ አንድ ጸሓፊ በሌላ ሥራ ውስጥ ተመዝግቦ የተገኘን የቃል ግጥሙ በራሱ ሥራ ውስጥ ሲመዘግብ በትክክል መገልበጥ ባለመቻሉ የሚፈጠር ነው። ሦስተኛ፣ ጸሓፍቱ በራሳቸው ሥራ ውስጥ ቀድመው የመዘገቧቸውን የቃል ግጥሞች በሌላ ሥራቸው ሲጠቅሱ ጊዜ በትክክል ባለመገልበጣቸው ምክንያትም ልውጠት ተከስቷል። የቃል ግጥሞቹ የሚታዩባቸው የቅርጽም፣ የይዘትም ልውጠቶች በየተመዘገቡበት ሥራ ውስጥ ለትውልድ መተላለፋቸውን ይቀጥላሉ።

በአንዳንድ ተለውጠው በተመዘገቡት የቃል ግጥሞች የምእላድ እና የቃል ልውጠት ይስተዋልባቸዋል። በአንዳንዶቹ የቃል ግጥሞች ደግሞ የሐረግ እና የሥንኝ አደራደር ልውጠት ይነበብባቸዋል። በሌሎቹ የቃል ግጥሞች የሐረግ እና የሥንኝ አደራደር ቅደም ተከተል ለውጥ፣ የሐረግ እና የሥንኝ መጨመር እና መቀነስ መኖሩን መገንዘብ ተችሏል። የተጠቀሱት ልውጠቶች በቃል ግጥሞቹ ላይ የቅርጽ ብቻ ሳይኾን፣ የቅርጽም፣ የይዘትም መለወጥ ያስከትላሉ። በቃል ግጥሞቹ የታዩት የይዘት ልውጠቶች ስለ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ በታሪክ ሰነዶች ከተመዘገበው ጋራ ሲመሳከሩ አንዳንዶቹ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የፈጸሙትን ድርጊት በምሉእነት ሲገልጹ አንዳንዶቹ ደግሞ ከፊሉን ይነግራሉ፤ ከታሪካዊ እውነታው የሚያፈነግጡም፣ የሚቃረኑም አሉ። ስለኾነም ተመራማሪዎች ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ከፈጸሟቸው ታሪካዊ ድርጊቶች የሚቃረኑ መልእክቶች የተላለፉባቸውን የቃል ግጥሞች በታሪክ ማስረጃነት ሲጠቀሙ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይገባቸዋል።

ለዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ የተዜሙ እና በተለያዩ ጸሓፍት ተለዋውጠው የተመዘገቡ የቃል ግጥሞች ኹሉም አልተመረመሩም፣ አልተተነተኑም። ከዚኸም በላይ ስለዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ በተዜሙት እና በጽሑፍ ባልተመዘገቡት የቃል ግጥሞች ልውጠት እንደሚኖር ቢታመንም በዚኽ ጥናት ትኩረት አልተደረገባቸውም። ስለኾነም፣ በዚኽ ጥናት ባልተመረመሩት በጽሑፍ በተመዘገቡት እና በቃል በሚተላለፉት ልውጠት እና ቅጥለት በሚታይባቸው ለዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ በተዜሙ የቃል ግጥሞች ላይ የፎክሎር፣ የሥነጽሑፍ፣ የታሪክ፣ የሥነ-ሰብእና እና ሌሎችም የሚመለከታቸው ተመራማሪዎች ትኩረት በማድረግ መመርመር በሙያ መስኩ ሊኖር የሚገባውን ዕውቀት ያሰፋል፤ ያጎለብታል። በተጨማሪም፣ የዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን የተለያዩ ድርጊቶች የሚደግፉ፣ የሚነቅፉ፣ አሚሚታቸውን የሚዘክሩ በርካታ የቃል ግጥሞች በጽሑፍ የተመዘገቡ፤ በቃልም የሚተላለፉ አሉ። በቃል የሚተላለፉትን እና በጽሑፍ የተመዘገቡትን የቃል ግጥሞች ማጥናት ተገቢ ነው። በቃል ግጥሞቹ የሚተላለፉትን መልእክቶች ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ከፈጸሟቸው ድርጊቶች ጋራ እያነጻጸሩ ማጥናት የታሪክን እና የቃል ግጥምን ትሥሥር ለመገንዘብ ያስችላል እና ተመራማሪዎች ትኩረት ሊያደርጉባቸው ይገባል። ስለ ዐፄ ዮሐንስ ፬ኛ፣ ስለ ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ፣ ስለ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፣ ስለ ተለያዩ መሳፍንት እና መኳንንት የተዜሙ የቃል ግጥሞችን ማጥናት ተመሳሳይ ጠቀሜታ ሊኖረው ይችላልና የሚመለከታቸው ተመራማሪዎች ትኩረት መስጠታቸው ተገቢ ነው ተብሎ ይታመናል።

መረጃ ጽሑፎች

መርዕድ ወልደ አረጋይ፡፡ (1990) (እ. ጎ. አ.)፡፡ የቴዎድሮስ ዓላማዎች ከየት እንደመነጩ፡፡ *Kasa and Kasa: Papers on the Lives, Times and Images of Tewodros II and Yohannes IV (1855-1889)*. (Edited by Taddese Beyene, Richard Pankhurst, and Shiferaw Bekele). Institute of Ethiopian Studies, pp. 69-115.

መስፍን መሰለ፡፡ (2022) (እ. ጎ. አ.)፡፡ ተለዋዋጭነት ለደጃዝማች ካሣ/ለዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ በተዜሙ ቃል ግጥሞቸች፣ ዑውዳዊ ትንተና፣ *ዜና ልሳን* ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ መጽሔት፣ XXXII (2), pp. 25-65፡፡

መስፍን መሰለ፡፡ (2018) (እ. ጎ. አ.)፡፡ የዐፄ ቴዎድሮስ ጀግንነት በአዝማሪ አንደበት፣ *ዜና ልሳን*፤ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ መጽሔት፣ XXVII (1), pp. 90-122.

መዝሙረ ዳዊት፡፡ (፲፱፻፹፪)፡፡ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፡፡

ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፡፡ (፲፱፻፷፩)፡፡ *አማርኛ ቅኔ ከነ መፍቻው ተሻሽሎና ታክሎበት የተሰናዳ*፡፡ (እንደገና የታተመ) አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፡፡ (፲፱፻፷፪)፡፡ *ዝክረ ነገር* ፡፡ ሴንተራል ማተሚያ ቤት፡፡

ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል፡፡ (1969 እ. ጎ. አ.)፡፡ የኢትዮጵያ ባህል ጥናት፡፡ ቼ በለው፡፡ *የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር መጽሔት* ፣ VII (2)፣ 199-303::

ሥርግው ሐብለ ሥላሴ፡፡ (2002)፡፡ *ዳግማዊ ምኒልክ የአዲሱ ሥልጣኔ መሥራች* ፡፡ (የታተመበት ቦታና ማተሚያ ቤት አልተገለጸም)፡፡

ሥርግው ገላው (ሐተታ)፡፡ (2008)፡፡ *የኢትዮጵያ ታሪክ*፡፡ (ተክለ ኢየሱስ ዋቅጅራ እንደጻፈው) ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

በዕውቀቱ ሥዩም፡፡ (2009)፡፡ መሰንቆና ብትር (ወግ)፡፡ አንድምታ የጥበብ መጽሔት፡፡ Retrieved at: https://andemta.com2017/06/02, accessed on November, 2019.

ባሕሩ ዘውዴ፡፡ (፪ሺህ)፡፡ *የኢትዮጵያ ታሪክ፤ ከ1847 እስከ 1983*፡፡ (ተሻሽሎ የታተመ) አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፡፡

ብርሃኑ አበበ፡፡ (፲፱፻፹)፡፡ የዘመነ መሳፍንት ግጥሞች፣ *የኢትዮጵያ ዓመታዊ የታሪክ መጽሔት*፣ ፲ኛ መጽሔት፣ ገጽ 13-38፡፡

ብርሃኑ አበበ፡፡ (፲፱፻፸፫)፡፡ በግጥም የተጻፈ ዜና መዋዕል አንቷን ዳባዲ እንዳቆየው፣ *የኢትዮጵያ ዓመታዊ የታሪክ መጽሔት*፣ ፫ኛ መጽሔት፣ ገጽ 35-44፡፡

ብርሃኑ አበበ፡፡ (፲፱፻፷፪)፡፡ "HAMINA DISTIQUES AMHARIQUES D'APRES UNE TRANSCRIPTION D'ANTOINE D'ABBADIE", *የኢትዮጵያ ዓመታዊ የታሪክ መጽሔት* ፡፡ ፳ኛ መጽሔት፣ Pp. 89-101፡፡

ተሰማ ሀብተ ሚካኤል ግጽው፡፡ (፲፱፻፶፩)፡፡ *ከሣቴ ብርሃን ተሰማ፡፡ የዐማርኛ መዝገበ ቃላት*፡፡ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፡፡ (፳፪)፡፡ *የኢትዮጵያ ታሪክ፣ ከዐፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ*፡፡ (እንደገና የታተመ) (ማተሚያ ቤቱ አልተገለጸም)፡፡

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፡፡ (፲፱፻፹፩)፡፡ *ዐፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት*፡፡ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት (ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት)፡፡

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፡፡ (፲፱፻፴፮)፡፡ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ፡፡* (የመጀመሪያ እትም) ብርሃንና ሰላም ቀ. ኃ. ሥ. ማተሚያ ቤት፡፡

ኀሩይ ወልደ ሥላሴ፡፡ (፳፻፩)፡፡ *የልቅሶ ዜማ ግጥም፤ መሥጢሩ ከመጻሕፍት ጋራ የተስማማ፡፡* (ኹለተኛ እትም) ኮምፒዩግራፊ አታሚዎች፡፡

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (1993)፡፡ *ኣማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡* አርቲስክ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፡፡ (2000)፡፡ *የመጽሐፍ ቅዱስ፤ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት፡፡* (ማተሚያ ቤቱ አልተገለጸም)፡፡

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፡፡ (፲፱፻፵፫)፡፡ *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ* ፡፡ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ደስታ ተክለ ወልድ፡፡ (፲፱፻፷፪)፡፡ *ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡* አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ዓለማየሁ ሞገስ ፡፡ (፲፱፻፷፯)፡፡ *የአማርኛ ሐረግ* ፡፡ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡፡

ዓለማየሁ ሞገስ ፡፡ (፲፱፻፶)፡፡ *የአማርኛ ግጥምና ቅኔ፤ ማስተማሪያ* ፡፡ ብርሃንና ሰላም የቀዳማዊ ኀይለሥላሴ ማተሚያ ቤት፡፡

ገሪማ ታፈረ፡፡ (1996)፡፡ *አባ ታጠቅ ካሣ የቋራው አንበሳ፡፡* (ኹለተኛ ዕትም)፤ Finfinne Printing and Publishingt S. C.

ገብረ ሥላሴ ወልደ አረጋይ:: (፲፱፻፶፱)፡፡ *ታሪክ ዘመን ዘ ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ፡፡* አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፡፡

Crummey, Donald. (1971). The Violence of Tewodros, *Journal of Ethiopian Studies*, 9 (2), pp. 107-125.

Crummey, Donald. (1969). Tewodros as Reformer and Modernizer. *The Journal of African History*, 10 (3), pp. 457-469.

Finnegan, Ruth. (1977). *Oral Poetry: Its nature, significance, and social context*. WIPf and Stock publishers: Cambridge University Press.

Fusella, Luigi. (1959). “La Cronaca dell' Imperatore Teodoro II di Etiopia in un manoscritto amarico, *Annali dell' Instituto Universitario Orientali di Napoli. Nuóva serie*, volume VII, pp. 63- 89.

Fusella, Luigi. (1958). La Cronaca dell' Imperatore Teodoro II di Etiopia in un manoscritto amarico, *Annali dell' Instituto Universitario Orientali di Napoli. Nuóva serie*, Volume VII, pp. 69-94.

Girma *Getahun. (2014). The Goğğam Chronicle by Aläqä Täklä Iyäsus WaqGera. (Translator). Oxford University Press.*

Littmann, Enno. (1902). *The Chronicle of King Theodore of Abyssinia*. (Editor). Otto Harrassowitz.

Pankhurst, Richard and Asfaw, Girma-Selassie. (1985). AN AMHARIC WAR-SONG OF EMPEROR TEWODROS' S SOLDIERS, *Journal of Ethiopian Studies*. 18, pp. 51-62.

Rubenson, Sven. (1966). *Kings of Kings Tewodros of Ethiopia*. Oxford University Press.

Taye Assefa. (1983). Téwodros in Ethiopian Fiction, *የኢትዮጵያ ጥናት መጽሔት Journalof Ethiopian Studies, Vol. XVI, pp*.115-128.

Venkataram, Krishnamurthy. (1973). Foreign Policy of Theodore II of Ethiopia: an Interpretation, *Transafrican Journal of History*, 3(1/2), pp. 129-145.

Vidailhet, Mondon C. (1904). *Chronique Theodoros II Roi des Rois d' ethipie (1853- 1863) d' apres un Manuscript Original Text Abyssin (Amharique*). (No place of publication and printing press).